## ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በኢትዮጵያ

# የሰቆጣ ቃል ኪዳን

## የባለድርሻ አካላት ትብብር እና ቅንጅት አተገባበር መመርያ



ሓምሌ 2011 ዓ.ም.

አዲስ አበባ:

ኢትዮጵያ

c4ie

**መቅድም**

የሰቆጣ ቃል ኪዳን እ.ኤ.አ. በ 2030 የህፃናትን የተመጣጠነ ምግብ እጥረት/መቀንጨርን/ ለማስቀረት በኢትዮጵያ መንግስት ቁርጠኝነት የተዘጋጀ መረሃ ግብር ነው:: ሰቆጣ ቃልኪዳን ስርዓተ ምግብ ለኢኮኖሚ ልማት ያለውን መሰረታዊ አስተዋፅኦ በመገንዘብ መንግሰት ለሰብዓዊ ልማት ያለውን ቁርጠኝነት ያረጋገጠበት ነው፡፡ ይህም የሚተገበረው በሁለተኛው ብሄራዊ የስርዓተ ምግብ ፕሮግራም (NNP II) ስር ነው:: በቀጣይ የ15 ዓመታት መረሃ ግብር ይህ ፕሮገራም በአማራ እና በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሚገኙና በተከዜ ተፋሰስ ከፍተኛ ተጽዕኖ በሚደርስባቸው 33 ወረዳዎች ይተገበራል:: ሁለተኛው የብሄራዊ ስርዓተ ምግብ እቅድ (NNP II) እና የሰቆጣ ቃልኪዳን መቀንጨርን ለመቀነስ የስርዓተ ምግብ ተኮር እና አካቶ(Nutrition specific and sensitive) የተባሉትን የመተግበሪያ ስልቶችን ትኩረት በማድረግ ይንቀሳቀሳሉ:: እነዚህ ስልታዊ አላማዎች እና ተግባራትም ሊፈጸሙ የሚችሉት በሰቆጣ ቃል ኪዳን ወረዳዎች የባለድርሻ አካለት ቅንጅታዊ አሰራር ብቻ ነው:: የባለድርሻ አካላት ተነሳሽነት እና ቁርጠኝነት የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን ለመቀነስ የሚስችል ሲሆን የሰቆጣ ቃል ኪዳን ዋና የትግበራ ዘዴም ነው ፡፡ቃል ኪዳኑ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ዘርፎች በርካታ ባለድርሻ አካላት ወደ ስራ ገብተዋል ፡፡ ከሰባት በላይ የመንግስት ሴክተሮች ፣ ለጋሽ ድርጅቶች ፣ ፈጻሚ አጋር አካላት (IPs) እና ሲቪል ማህበረሰብ (CSOs) በሃገር፣ በክልል እና በወረዳ ደረጃዎች የሰቆጣ ቃል ኪዳን ባለድርሻ አካላት ናቸው ። ሆኖም የባለድርሻ አካላት ትብብር እና የአጋርነት አስተዳደር ስርዓት (MSCPM) ቢኖርም በሰቆጣ ቃል ኪዳን መረሃ ግብር ላይ ትልቅ ክፍተት ነበር ፡፡

በንዑስ ብሄራዊ ደረጃ የባለድርሻ አካላትን ቅንጅትና ትብብርን ለማጠናከር የባለድርሻ አካለትን አጋርነት እና ቅንጅት መመሪያ (MSCPM) እና አጋዥ መጠቀምያ መሣሪያዎች ተዘጋጅተዋል ፡፡ ይህ መመሪያ የወረዳ እና ክልል የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካላትን እና የቴክኒክ ኮሚቴዎችን ወደ ስራ ለማስገባት ይረዳል:: የተሸሻለ የባለድርሻ አካላት ቅንጅት ለስርዓተ ምግብ መረሃ ግብር ውጤታማ ትግበራ እና ትብብር አስተዋፆ ከማድረጉም በላይ አሁን ያለውን የስርዓተ ምግብ ችግር እንዲሻሻል ያደርጋል:: ይህ መመሪያ የአስተባባሪ አካላትን ለመቆጣጠርና ባለድርሻ አካላትን ለማሳተፍ፣ እድገትን ለመለካት፣ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እና የፕሮግራሙን የባለቤትነት መንፈስ በመጨመር

ዘላቂ የሆነ የስርዓተ ምግብ አገልግሎት እንደሚያሳድግ ይታመናል:: ከዚህ ጋር ተያይዞ ግንዘቤ ውስጥ የሚገባው የሰቆጣ ቃል ኪዳን ልምድ ማጎልበችያ ምርዓፍ እንደ መሆኑ መጠን መመሪያው ከባለድርሻ አካላት ጠቃሚ ሃሳብ ጋር በሚጣጣም መልኩ እንደሚሻሻል መታወቅ አለበት:: ይህ መመሪያ ከሰቆጣ ቃል ኪዳን ወረዳዎች እና ከክልል መንግስታት ባሻገር ለሌሎች አካላትም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ፡ ፡ በመሆኑም የመረሃ ግብሩን ተግባራት ለማሳወቅና ቀጣይና መደበኛ ለማድረግ፣ በተለይም በሁሉም ደረጃ በማስረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔዎችን ለመተግበር እና በአጠቃላይ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ግቦችን እንዲሳኩ ለማድረግ ይህን መመሪያ እንዲጠቀሙ እንመክራለን ፡፡

## ምስጋና

ይህ የባለድርሻ አካላት ቅንጅት እና አስተዳደር (MSCPM) መመሪያ የተዘጋጀው በፌደራል፤ በአማራ እና ትግራይ ክልል ሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራም ማስተባበሪያ ክፍሎች፤ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪና ቴክኒክ ኮሚቴዎች፤ ጽ/ቤቶች፤ የሁለቱ ክልል ር/መስተዳድር አማካሪዎች እና ደጋፊ አካላት ሙሉ ተሳትፎ ነው፡፡ የአማራና ትግራይ ክልል ርዕሳነ መስተዳድሮች በዚህ መመሪያ ዝግጅት ወቅት በሚመለከታቸው አጋር አካላት አስፈላጊ የሆነውን ውይይት እንዲካሄድበት ምቹ ሁኔታ ስለፈጠሩ ምስጋና ይገባቸውል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሰትም አጋር አካላት ለሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራም ያደረጉትን የቴክኒክና ፋይናንስ አስተዋፅኦ/ድጋፍ/ እውቅና ይሰጣል፡፡ ይህ የዘርፈ ብዙ ባለድርሻ አካላት ቅንጅት እና አጋር አካላት አስተዳደር (MSCPM) መመሪያ የተዘጋጀው በThuraisingham Associates; c4ie LLC እና Nitsuh Ethiopia consortium ሲሆን ለዚህም የፋይናን ድጋፍ ያደርገው የእንግሊዝ አለማቀፍ ተራድኦ ድርጅት በአለማቀፍ ስርዓተ ምግብ ድርጅት በኩል ስለሆን ምስጋና ማቅረብ እንወዳለን፡፡

ሠንጠረዥ

1. መግቢያ ............ 6
1.1 ለመመሪያው ዝግጅት መነሻ ምክኒያቶች ............ 6
1.1.2. የመመርያዉ ቀጣይነት ............ 8
1.1.3. ቅንጅታዊ አሰራርና ስርዓት ያታ ............ 8
1.1.4. የመመሪያው ዓላማና ወሰን ............ 10
1.1.4.1. የመመሪያው ዓላማዎች ............ 10
1.1.4.2. የመመሪያው ወሰን ............ 11
1.1.4.2. የመመሪያው አጠቃቀም ............ 12
1.1.4.3. የመመርያው መዋቅር ............ 12
1.2 በክልልና በወረዳ ደረጃ ባለ ዘርፍ ብዙ ባለድርሻ አካላት ቅንጅት እና ባለድርሻ አካላት አስተዳደር ለምን ያስፈልገል? ............ 13
1.3 የባለድርሻ አካላት ቅንጅትና የአጋርነት አስተዳደር ዋና ዋና መርሆዎች ............ 14
13 የባለብዙ ባለድርሻ አካላት ቅንጅትና የአጋርነት አስተዳደር ............ 15
2. የባለ ድርሻ ኣካላት አስተዳደር ስርዓት ............ 16
2.1 የመመሪያው አተገባበር ስልት ............ 18
2.1.1 የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል (WNCB) ስብጥር ............ 20
2.1.2 የወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ ስብጥር ............ 22
2.2 በክልል ደረጃ የዘርፈብዙ ባለድረሻ አካላት ቅንጅት እና አጋር አካላትን ትብብር ............ 27
2.2.1. የክልሉ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል የአባላት ስብጥር እና ሃላፊነት ............ 28
2.2.2. የክልሉ የስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ ስብጥር፣ የስራድረሻ እና ኃላፊነት ............ 29
3. ቅንጅዊ አሰራርን ለመምራት የምንጠቀምባቸው አሰራሮችና መተግበርያ መሳርያዎች ............ 30
4. የክትትል እና ግምገማ አመልካቾች ............ 31
አባሪወች ............ 34
አባሪ ሀ: ............ 34

አባሪ ለ:......36
አባሪ ሐ:......37
አባሪ መ:......38
አባሪ ሠ:......39
አባሪ ረ:......40
አባሪ ሰ:......41
አባሪ ሸ......42
አባሪ ቀ:......44
አባሪ በ:......46
አባሪ ቸ:......46
ባለድርሻ አካላት ስራ አመራር መረጃ ቻት......46
ማጣቀሻ:......49
ቁልፍ ውሎች የቃላት:......50

## 1. መግቢያ

### 1.1 ለመመሪያው ዝግጅት መነሻ ምክኒያቶች

ሰቆጣ ቃል ኪዳን ከሁለት አመት በታች ያሉ ህፃናትን የመቀንጨር ችግር ለመቅረፍ ሰኔ 2007 ዓ.ም በመንግሰት የታወጀ የቃል ኪዳን ሰነድ ነው፡፡ ይህ አገራዊ የልማት ዕቅድ በአገራችን ያለዉን የስርዓተ ምግብ ፕሮገራም መሰረት በማድረግ የተቀረፀ ሲሆን የህፃናትን የመቀንጨር ችግር በ2022 ዓ.ም ለማስወገድ ግብ አስቀምጧል፡፡ ለመርሃ ግብሩ መሳካት በተከዜ ተፋሰስ በሚገኙ 33 የአማራ እና የትግራይ ወረዳወች ለ15 ዓመታት የሚፈጸም እና ለተግባራዊነቱ ሁሉም አካላት እንዲሳተፉ ይጠበቃል፡፡

የሰቆጣ ቃል ኪዳን ስርዕተ ምግብ ተኮርና ተዛማጅ የሆኑ ተግባራት ፈጻሚ የመንግሰት ተቋማት ተለይተዋል፡ ፡ እነዚህም ጤና፣ ግብርና፣ ትምህርት፣ የዓሳና እንስሳት ሃብት ልማት፣ የዉሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ኢነርጂ ፣ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ እና ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ ማህበረሰብ ተቋማት፣ የሃይማኖት ተቋማት እና የግል ድርጅቶች የሰቆጣ ቃል ኪዳን ደጋፊ እንደሆኑ ይታመናል፡፡

በ15 ዓመታት እንዲፈጸም የሚጠበቀው ሰቆጣ ቃል ኪዳን በሶስት ምዕረፍ የተከፈለ ነው፡፡ የመጀመሪው ምዕራፍ የሙከራ ጊዜ (ከ2008-2012 ዓ.ም) ሁኖ በዋናነት ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራትን መሰረት ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ፕሮገራሙን ለማስፋት የሚያስችል ግብዓብት ማሰባሰብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የማስፋፋት (ከ2013 -2017 ዓ.ም) ለህጻናት መቀንጨር የተጋለጡ ተጨማሪ ወረዳዎች በፕሮግራሙ የሚካተቱበት ጊዜ ነው፡፡ በሶስተኛው ምዕራፍ (2018 -2022 ዓ.ም) ሰቆጣ ቃል ኪዳን ተሞክሮዎችን መሰርት ባደረገ እና ዘርፈ ብዙ በሆኑ ሁኔታዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባረዊ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ አስር ዋና ዋና ስትራቴጂክ ዓላማዎችና ሃምሳ ተገባራት በ33 ወረዳወች ማለትም በ27 የአማራ ክልል እና በ6 የትግራይ ክልል ወረዳወች ይከናዎናሉ

(የቃልኪዳኑ ዋና ዋና ዓላማዎች በአባሪ ክፍል ተያይዘዋል)፡፡ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ውጤታማነት በአጋር አካላት የተጠያቂነት አሰራር እና የማስተባበር ብቃት ላይ ይወሰናል፡ ፡

የዚህ መመሪያ መዘጋጀት መሰረታዊ ምክኒያት የሰቆጣ ቃል ኪዳን ዓላማዎች ለማሳካት ጥረት የሚያደርጉ ልዩ ልዩ አጋር አካላትን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል ስልት ለመዘርጋት ነው፡፡

መመሪያው የተዘጋጅው በክልልና በወረዳ ደረጃ የስርዓተ ምግብ ተግባራትን ለሚያስተባብሩ ወይንም ለሚመሩ፣ የቴክኒክ ኮሚቴዎች፣ ጽ/ቤቶችና ቢሮዎች እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን ውጤታማ የሆነ የማስተባበር ስርዓት እንዲኖራቸው ነው፡፡

ውጤታማ የሆነ የማስተባበር እና የመረጃ አያያዝ ሥርዓት የሚኖረው ፋይዳ

- ዘርፈ ብዙ የሆኑ ተቋማት የሰቆጣ ቃል ኪዳን አላማዎችን በወቅቱ እንዲፈጽሙ ይረዳል፣
- በመረጃ ላይ የተደገፈ ውሳኔ ለማሳልፍ የሚዉል ግብዓት ለማሰባሰብ ያግዛል፣
- ያሉንን ሃብትና ዕውቀት/ክህሎት በአግባቡ ለመጠቀም ይረዳል፣
- ያሉንን ሀብት ለማወቅና መረጃን መሰረት ያደረገ የሀብት ምደባ ለማድረግ ይረዳል፣
- ሃብትን በአግባቡና በወቅቱ ለመጠቀም እንዲሁም ክፍተቶችን በመለየት ተጨማሪ ሃብት ለማምጣት ይረዳል፣
- የሰቆጣ ቃል ኪዳን ዋና ዋና ዓላማዎችና እና ቁልፍ ተግባራትን ለመደገፍ ይጠቅማል፣
- ተጨማሪ ሃብት ለማሰባሰብ እና ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ መረጃን መሰረት ያደረገ ውይያት እና ዉሳኔ እንዲኖር ይረዳል፣
- ስርዓት ፆታን መሰረት ያደረገ ዕቅድና የበጀት ምደባ እንዲኖር ይረዳል፣
- በሁሉም ሰቆጣ ቃል ኪዳን ወረዳወች አካባቢ ፍትሃዊ የሆነ የስርዓተ ምግብ አገልግሎትን ለመዘርጋት ይጠቅማል

ስለዚህ ይህ መመሪያ በክልል እና በወረዳ ደረጃ አሁን ያለውን ባለድርሻ አካላት አሰራር እና የማስተባበር ሁኔታን ለማጠናከርና ወጥ ለማድረግ ያለመ ነው፡፡ በክልልም ይሁን በወረዳ ደርጃ ውጤታማ በሆነ መልኩ ባለድርሻ አካላት ለማሰተባበር ሁሉም ወረዳዎች፣ የክልል ቢሮዎች እና የፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍል መመሪያውን ተግባራዊ ማድረግ

ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሰቆጣ ቃል ኪዳን በፌደራል ደረጃ ያሉ ሚኒስተር መስርያቤቶች፣ የ ቃልኪዳኑ የፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍል እና ሌሎች አጋር አካላት ሃብትን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል የአሰራር ስርዓቶችን ስራ ላይ ለማዋል እንዲቻል ክልሎችን እና ወረዳዎችን ለመደገፍና ተገቢውን እገዛ ለማድረግ ይህን መመሪያ ይጠቀሙበታል፡፡ መመሪያውም ከሰቆጣ ቃል ኪዳን እስትራቴጂክ ዓላማዎች ዉስጥ "የተቋማትን ቅንጅታዊ አሰራርና የመፈፀም አቅም ማሻሻል" ከሚለው እስትራቴጂክ ዓላማ ቁጥር አስር መሰረት ያደረገ ነው፡፡

### 1.1.2. የመመርያዉ ቀጣይነት

የቅንጅት አሰራሮችን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ለአገራዊ ስርዓተ ምግብ ፕሮገራም ማስፈጸሚያ የተቀረፁ አደረጃጀቶችንና ተያያዥ መመሪዎችን መሰረት አድርጎ መፈጸም ይገባል፡፡ በስርዓተ ምግብ ዙሪያ ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በተመለከተ አዲስ አደረጃጀትም ሆነ አሰራር የመመስረት ሳይሆን አሁን ያለውን የማጠናከርና የማደራጀት እንዲሁም አደረጃጀቶች በሌሉበት እንደገና እንዲቋቋም አስፈላጊው የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፡፡ ይህም በክልልና ወረዳ ደረጃ በተመሳሳይ ሁኔታ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ቅንጅታዊ አሰራር የሚኖረውን ውጤታማነት ለመለካት በአገር ደረጃ የተለዩ የስኬት አመላካቾችን ስራ ላይ ማዋል ይጠበቃል፡፡ በየደረጃው ያሉ አጋር አካላትን መደገፍና ተገቢውን የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠት ይህ መመሪያ ተፈጻሚ እና ዘላቂ እንዲሆን ያግዘዋል፡፡

የሰቆጣ ቃል ኪዳን የአገር አቀፍ ስርዓተ ምግብ አካል በመሆኑ ዓላማዎቹንና ተግባራቱን ለማስፈፀም፣ ተገቢዉን ሃብት ለመመደብ እንዲሁም ተጠያቂነትን ለማስፈን የነበረዉን አደረጃጀት በመከተል ነው፡፡ ስለሆነም በክልልና በወረዳ ደረጃ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የቴክኒካል ኮሚቴ ከዚህ በፊት የነበረዉ አደረጃጀት የሚቀጥል ይሆናል፡፡ የእነዚህ አደረጃጀቶች አወቃቀርና አሰራር አገራዊ የማስፈጸሚያ ስልቶችን እና አቅጣጫዎችን የሚከተል ይሆናል፡፡

### 1.1.3. ቅንጅታዊ አሰራርና ስርዓተ ፆታ

የሰቆጣ ቃል ኪዳን ዓላማዎችንና የአገር አቀፍ ስርዓተ ምግብ ፕሮገራም ዝርዝር ዕቅዶችን ለማሳካት ስርዓተ ፆታን ማካተት ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ የስርዓተ ፆታ ጉዳይ

የቅንጅታዊ አሰራር አካል ሁኖ መታየት አለበት፡፡ ቅንጅታዊ አሰራርን ለማጠናከር የተቋቋሙ አደረጃጀቶች የፆታ ተዋፅኦን ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን አለባቸው፡፡ ቅንጅታዊ አሰራርን ለማጎልበት የተቋቋሙ ልዩ ልዩ አደረጃጀቶችን እየመሩ ያሉ አካላትም በጋራ እቅድ ዝግጅትና ግምገማ እንዲሁም በሃብት አመዳደብ ወቅት የፆታ ተኮር አሰራር እንዲኖር ማዲረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የትኛውም የፕሮጀከት አተገባበር ፆታ ተኮር የሆኑ ውጤቶችን ማስመዝገባቸውን ማረጋገጥ ይጠበቃል፡፡ አዳዲስ ፕሮጅክቶችም ቢሆኑ ፆታ ተኮር ተግባራትን ከማቀድ ባለፈ ተገቢውን የአፈፃፀም መለኪያዎች ማሰቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በየደረጃው ያሉ አስተባባሪ አካላትም ለሴቶች እኩልነትና ተጠቃሚነት ተገቢውን የማጠናከሪያ ስልጠና ማግኘት አለባቸው፡፡ ከዚህ በታች የተጠቀሱት የሰቆጣ ቃል ኪዳን ስትራቴጂክ ዓላማዎች ስርዓተ ፆታን ያገናዘበ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ያግዛሉ፡፡

- ከሁለት ዓመት በታች ያሉ ህፃናትን፣ ሴቶችንና ታዳጊዎችን የጤናና የስርዓተ ምግብ ሁኔታ ማሻሻል
- የነፍሰ ጡርና የሚያጠቡ እናቶችን እንዲሁም የህጻናትን የስርዓተ ምግብ ሁኔታ ለማሻሻል የምግብ ዋስትና ተግባራትን መፈፀም
- የሴቶች ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እና አቅም ማጎልበት እንዲሁም የህፃናት ጥበቃን ማሻሻል

በተጨማሪም በአገራዊ ስርዓተ ምግብ ፕሮገራም ዕቅድ ዉስጥ በስትራቴጅክ ዓላማ ቁጥር አራት (4.11) እንደተገለፀው ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ የስርዓተ ምግብ እቅድ አዘገጃጀት እንዲኖር ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን ዓላማ አንድ(1)ና ሁለት(2) የስርዓተ ፆታ ተኮር ስርዓተ ምግብ ትግበራን የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ የማህበረሰብ ጤና ተቋም ያሉ ድርጅቶች የስርዓተ ፆታ ተኮር አሰራርን (Gender mainstreaming) የፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ ቁልፍ የሆነ ስልት መሆኑን በመግለፅ የፆታ እኩልነት በፖሊሲ ዝግጅት፣ በህግ ዝግጅት፣ በጥናትና ምርምር፣ በሃብት ምደባ፣ በዕቅድ ዝግጅትና ግምገማ ወቅት ሊታለፍ የማይችል ጉዳይ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም የእናቶችና ህፃናት እንክብካቤ የህጻናትን ስርዓተ ምግብ ለማሻሻል የሚጠቅም ቁልፍ መመዘኛ እንደሆነ ይታመናል፡፡ የህፃናትና ታደጊዎች የአመጋገብ ስርዓት፣ ጡት ማጥባት እና ተጨማሪ ምግብ መመገብ ዋናዋና የእንክብካቤ ስልቶች መሆናቸውን መረዳት ይገባል፡፡

#### 1.1.4. የመመሪያው ዓላማና ወሰን

##### 1.1.4.1. የመመሪያው ዓላማዎች

አገራዊ የስርዓተ ምግብ ፕሮግራምን መሰረት በማድረግ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራምን የሚደግፉ ባለድርሻ አካላትን ማለትም በወረዳና በክልል ደረጃ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶችን የሚፈጽሙና ግብረ ሰናይ ድርጅቶችን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተባበር እንዲቻል ነው፡፡ በተጨማሪም የሰቆጣ ቃል ኪዳንን መሰረት በማድርግ በክልልና በወረዳ ደረጃ የመረጃ ግብዓት፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ሃብት አሰባሰብ፣የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መስተጋብር፣ አፈፃጸምና ተጠያቂነትን ለማሳለጥና ስኬታማ ለማድረግ ነው፡፡

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አባላትን ስብጥር ግልፅ በማድረግ ቅንጅታዊ ስራ ማስፈንና ወጥ የሆነ የማስተባበር ስርዓትን መዘርጋት እንደመሆኑ የነዚህን ተቋማት ተግባርና ሃላፊነት፣ የመረጃ ልዉዉጥ ዘዴ፣ በአሳተባባሪና ቴክኒክ ኮሚቴ እና ባለድርሻ አካላት መካከል የሚኖረውን የግንኙነት አግባብ እንዲሁም የመረጃ አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ ግልፅ ያደርጋል፡፡ ይህ ቅንጅታዊ አሰራር በሚተገበርበት ጊዜ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ተግባር አፈፃጸም ይሳለጣል፣ውጤታማ የሆነ ሃብት አጠቃቀምን ለመከታተል ያግዛል፣ እንዲሁም የባለድርሻ ኣካላትን ሙሉ መረጃ ለመያዝ ይረዳል፣ ባጠቃላይ ይህን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያሰገኛል::

- የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራምን አፈፃፀም በጋራ ለመገምገም፣
- ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥና የሰራ ድግግሞሽ ለመቀነስ፣
- በሰቆጣ ቃል ኪዳን ወረዳዎች ሃብት እንዳይባክንና ተግባራትን በአግባቡ ለመሰነድ፣
- ወቅታዊ የሃብት አጠቃቀምን ለማጎልበት፣ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ተግባራትን በመለየት በበጀት ለመደገፍ፣
- የሃብት አጠቃቀምን፣ ቅንጅታዊ አሰራርን እና የመረጃ ቋት በየጊዜው ለማሻሻል (ለማዘመን)
- በሰቆጣ ቃል ኪዳን ወረዳዎች መረጃ ለማሰባሰብ፣ ልምድ ለመለዋዎጥ፣ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለመለየት እና ለማደራጀት፣
- በመረጃ ላይ የተደገፈ ውሳኔ በሁሉም ደረጃ ለመስጠት፣
- ለስርዓተ ምግብ ተጨማሪ ሃብት ለማሰባሰብ፣

- የሰቆጣ ቃል ኪዳን ትግባራት ውጤታማና ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣
- የሃብት ተገማችንትን ለማሻሻል፣ እንዲሁም ያልተጠበቀ የበጀት እጥረትን ለመከላከል፣
- የአከባቢዉን ሁኔታ ያገናዘበ ፈጠራን፣ መረጃ አያያዝን እና የተሻለ ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ ትግባራን ለይቶ ለማስፋፋት፣

**የክልልና የወረዳ ቅንጅታዊ አሰራር ማዕቀፍ**

**ራዕይ**፡ ክልሎችና ወረዳዎች የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮገራም ዓላማዎችን አሳክተው ማየት።

↓

**ግብ፡** ክልሎችና ወረዳዎች የሰቆጣ ቃል ኪዳን የዘርፈ ብዙ ባለድረሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ።

↓

**ዉጤት**፡ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ክልሎችና ወረዳዎች የአጋር አካላት ውይይቶችን ሲያካሂዱና ወቅታዊ የአጋር አካላት ቁመና የሚያሳይ መረጃ ሲይዙ፣ ቁልፍ የሆኑ ተቋማት በቅንጅታዊ ስራ አመራር ዙሪያ ሲሰለጥኑና ክህሎት ሲኖራቸው፣ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮገራም ዉጤቶች ለመለካት የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ተዘጋጀቶ ተግባራዊ

### 1.1.4.2. የመመሪያው ወሰን

የዘርፈ ብዙ ባለድረሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር መመሪያ የተዘጋጀው በክልልና በወረዳ ደረጃ መረጃን መሰረት ያደረገና ውጤታማ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ተግበርን ለማስተባበር እንዲቻል ሲሆን በዋናነት ለሚከተሉት ባለድረሻ አካላትን የተዘጋጀ ነው፡፡

- ለአስተዳዳሪዎች (ወረዳ፣ ክልል እነዲሁም የክልል አማካሪዎችን ጨምሮ)
- ለስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል

- ለስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ
- ለክልል ቢሮዎች
- ለወረዳ ጽ/ቤቶች
- ለግብረ ሰናይ ድርጅቶች (ለአገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ድርጅቶች)
- ለፈፃሚ አካላት
- ለግል ተቋማት፣ የእምነት ተቋማት እና የትምህርት ተቋማት
- ለክልል እና አገር አቀፍ ፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍሎች

#### 1.1.4.2. የመመሪያው አጠቃቀም

መመሪያው ቅንጅታዊ የአሰራርና የማሰተባበር ስርዓትን ለማጠናከር /ለማሻሻል/ የሚጠቅም ሲሆን በተለይም ለወረዳ አስተዳዳሪዎችና ለክልል ሃላፊዎች በቅንጀታዊ አሰራር ዙሪያ ግልፅነትን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም በወረዳ ጽ/ቤቶችና ክልል ቢሮዎች ላይ ያሉ የስርዓተ ምግብ ተጠሪ ባለሞያዎች እንዲሁም ሁሉም የስርዓተ ምግብ አጋር አካላት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ በዚህ መመሪያ የተገለፁ አሰራሮች ቅንጅታዊ ስራ አመራርን ከማጠናከር ባሻገር ሁሉም የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካላት እና የወረዳ ስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴዎች የአጋር አካላትን መረጃ ለመያዝና ትንታኔ ለመስጠት ይጠቅማል፡፡ መመሪያው አፈፃፀምን በመለካትና የሃበት አጠቃቀምን በመተንተን ከቅንጅታዊ አሰራር ውጤታማነትና ተጠያቂነት አንፃር ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን ለማወቅ እና እንዴት የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍን መጠቀም እንዳለብን መረጃ ይሰጣል፡፡

በተጨማሪም የሰቆጣ ቃል ኪዳን ፕሮግራምን ቅንጅታዊ አሰራር የሚያሳይ በድህረ ገፅ የተደገፈ የመረጃ ቋት (on-line partnership management database) የክልልና የወረዳን አጠቃላይ አፈፃፀም ያሳያል፡፡

#### 1.1.4.3. የመመርያው መዋቅር

ይህ መመሪያ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፈሎ የተዘጋጀ ሲሆን እነሱም

- የባለድርሻ አካላት ቅንጅት መሠረታዊ መመርያ፣ እና
- ለባለድርሻ አካላት የምንጠቀምባቸው የመተግበርያ ስልቶችን ያካተተ ነው፡፡

የሰቆጣ ቃል ኪዳን ባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ እና ባለድርሻ አካላት  አመራር መዋቅር

**ክልል**
- የክልል ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል (RNCB)
- የክልል ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ (RNTC)

**ዞን**
- የዞኑ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል (ZNCB)
- የዞኑ ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ (ZNTC)

**ወረዳ**
- የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል (WNCB)
- የወረዳ ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ (WNTC)

### 1.2 በክልልና በወረዳ ደረጃ ባለ ዘርፍ ብዙ ባለድርሻ አካላት ቅንጅት እና ባለድርሻ አካላት አስተዳደር ለምን ያስፈልገል?

እንደተባበሩት መንግስታት የስርዓተ ምግብ ቋሚ ኮሚቴ ዘገባ UN's Standing Committee on Nutrition (SCN) ከሆነ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ለበሽታ መከሰት ትልቅ አስተዋፆ የሚያደርግ እና የትምህርት ውጤት በመቀነስ፣ የአዋቂዎችን ገቢ ዝቅ በማድረግ፣ በሽታ የመከላለከል አቅምን በመቀነስ እና ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ህጻናት እንዲወልዱ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡ (የአለም ምግብ ፕሮገራም፣ 2014)

የባለድርሻ አካላት ቅንጅት ለመፍጠር የመንግስትንና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ከተለያዩ ሴክተሮች የተወከሉ የተለያዩ የመንግስት ሚኒስተር መስሪያ ቤቶች በልዩ ልዩ አጋር ድርጅቶች በመደገፍ  የስርዓተ ምግብ ችግርን ለማሻሻል በመንግስት መሪነት እየተደረገ ያለውን ጥረት ለማጠናከር ተናብበው መሰራት ያስፈልጋል፡፡ ከእነዚህም አካላት ውስጥ በተባበሩት መንግስታት እገዛ የቴክኒክ ድጋፍ ለየሃገራቱ የሚሰጡ ኤጀንሲዎች፣ በአገራዊ ልማት የሚሳተፉ ለጋሽ ድርጅቶች፣ ለችግሩ የተጋለጡ ወገኖች መደገፋቸውን የሚከታተሉ  ከህብረተሰቡ ጋር በቅርበት ከሚሰሩ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ሰርዓተ

ምግብን ለማሻሻል የሃብት አቅም ያለቸው የንግዱ ማህበረሰብ እና ከስርዓተ ምግብ ጋር በተዛመደ ስልጠናና ምርምር ላይ የሚሳተፉ የትምህርትና ሳይንስ ተቋማት ይገኙበታል፡፡

እንደ ባለድረሻ አካላት ቅንጅት የደሰሳ ጥናት ውጤት እና ባለድርሻ አካላት  አስተዳደር ተግባራዊነት ትንተና ጥናት ውጤት ከሆነ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ ኮሚቴ እና የወረዳ ሥርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ የሚመለከታቸዉ ባለድረሻ አካላትን ያካተቱ አይደሉም፡፡ የሲቪክ ማኅበራት እና ሌሎች ፈፃሚ አጋር አካላት የኮሚቴ አባል በመሆን አልተካተቱም፡፡ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተከናወኑ አንዳንድ ጥረቶችና ትግበራዎች በአግባቡ አልተሰነዱም፡፡ በአካባቢ የተገኙ ማስረጃዎች ስልታዊ በሆነ መንገድ ተተንትነው ለድጋፍና እገዛ ስራ ጥቅም ላይ አልዋሉም፡፡ ስለሆነም ይህ መመሪያ እያንዳንዱ የሰቆጣ ቃል ኪዳን ወረዳዎች በአካባቢ የተገኙ መረጃዎችን ስልታዊ በሆነ መንገድ በመተንተን ለወረዳ፣ ለክልል እንዲሁም ለፌደራል ተወካይ ወቅቱን የጠበቀ መረጃ ለመስጠት ይረዳል፡፡

የፓርላማ አባላትም ያላቸውን ኃላፊነትና ቁርጠኝነት በመጠቀም ለስርዓተ ምግብ ፕሮግራም አፈጻፀም ወሳኝ ሚና መጫወት ይገባቸዋል፡፡ ከፌደራል ፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍል ጋር በመደጋገፍ ከሰቆጣ ቃልኪዳን ወረዳዎች የተውጣጡ ተወካዮችም ክፍተቶችን ፈትሸው የማምጣት እና የፖሊሲ አዘጋጆችን እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ተዋናዮችን ትኩረት የሚስብ በአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ የድጋፍ ማእቀፍ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በሁለተኛው የብሄራዊ ስርዓተ ምግብ ፕሮግራም ስትራቴጂ ላይ እንደተገለፀው  የባለድርሻ አጋርነት ስልት በአምስቱ የስርዓተ ምግብ አሰራር መርሆዎቸ ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡ ግልፀኝነትና ተጠያቂነት፣ የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ የጋራ መግባባትና ትብብር መፍጠር፣ ፈጣን አገልግሎት መስጠት እና የፋይናንስ አቅምን ማጎልበት አምስቱ የስርዓተ ምግብ አሰራር መርሆዎቸ መሰረቶች ናቸዉ

## 1.3 የባለድርሻ አካላት ቅንጅትና የአጋርነት አስተዳደር ዋና ዋና መርሆዎች

በፓሪስ መግለጫ (Paris Declaration) እና በአክራ የድርጊት መርሃግብር (Acra Call for Action) መሰረት ውጤታማነት ላይ ያተኮረ የድጋፍ ስልት እና ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ እገዛዎች የማንኛውም ባለድርሻ አካላት ዉጤታማ አስተዳደር መነሻና ቁልፍ መርሆዎች

ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የዘርፈ ብዙ ባለድርሻ አካላት ቅንጅት እና ባለድርሻ አካላት አስተዳደር ሶስት ቁልፍ መርሆዎች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል፡፡

**ባለቤትነት**

- በክልል፣ በዞን እና በወረዳዎች የባለቤትነት መብት
- የአካባቢዉን ሁኔታ ያገናዘበ ስርዓትና ሂደቶች
- የባለድርሻ አካላት ቁመና

**ግልጸኝነት**

- ማቀናጀት/ማስተባበር/
- ግንኙነት/ የመረጃ ልዉዉጥ
- ወቅቱን የጠበቀ አጀንዳ መቅረፅ
- መደበኛ ስብሰባ
- ሰነዶች(ጋዜጣ፣ ቃለ ጉበኤ

**ተጠያቂነት**

- የአፈፃፀም ማሳያ ደሽ ቦርድ
- ቁጥጥር እና ግምገማ
- በማስረጃ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ (የሃብት ትንታኔ)
- የአፈጻጸም ግምገማ

### 13 የባለብዙ ባለድርሻ አካላት ቅንጅትና የአጋርነት አስተዳደር

አሁን ያለበት ሁኔታ፡ ባለድርሻ አካላት አስተዳደር ሥርዓት የባለድርሻ አካላት ውጤታማ ተሳትፎ እንዲኖርና የሰቆጣ ቃል ኪዳን የማስፈፀምያ ስልቶች በተሳካ ሁኔታ እንዲተገብሩ የሚያደርግ ቁልፍ መንገድ ነው፡፡ በመስከረም 2011 የተካሄደው የዳሰሳ ጥናት /rapid assessment/ እና በመጋቢት 2011 የተከናወነ ባለድርሻ አካላት ቅንጅት እና ባለድርሻ አካላት አስተዳደር የትግበራ ሁኔታ ጥናት ላይ ለመገንዘብ እንደተቻለው ምንም እንኳን የወረዳ ስርዓት ምግብ አስተባባሪ አካል እና የወረዳ ስርዓት ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ በአብዛኞቹ ወረዳዎች የተቋቋመ ቢሆንም የሚጠበቅባቸውን ያህል እየሰሩ እንዳልሆነ ለመረዳት ተችላል ፡፡ የወረዳ አስተዳዳሪዎች እና የወረዳ የስርዓት ምግብ ተጠሪዎችም የተቋቋሙት ኮሚቴዎች በሚፈለገዉ ደረጃ እየሰሩ እንዳልሆነ ያምናሉ፡፡

ተመሳሳይ ቅንጅታዊ አደረጃጀት የሚጠበቅባቸው ወረዳዎችም ከዚሕ በታች የተዘረዘሩት የሚከተሉት ውስንነቶች እንዳለባቸው ይህ ጥናት ያመላክታል፡፡

- የወረዳ ስርዓት ምግብ አስተባባሪ አካል እና የወረዳ ስርዓት ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴዎች የሚጠበቅባቸውን የህል እየሰሩ አይደለም፣ መደበኛ የስብሰባ ጊዜም የላቸውም፣
- የተከናወኑ ተግባሮችም መለኪያ መስፈርት የላቸውም፣

- የሚያካሂዱቸዉ አንዳንድ ስብሰባዎች በቃለ-ጉበኤ የሚመዘገቡ አይደሉም፣
- የኮሚቴው አባላት ስበስብ ወይም አወቃቀር ከወረዳ ወረዳ ይለያያል፣
- ባለድርሻ አካላት  አስተዳደር ሂደቱ  ወጥነት የለውም፣
- ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ እና የሃይማኖት ተቋማት በወረዳ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና በወረዳ የስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ ውስጥ በሚፈለገዉ መጠን ዉክልና አላገኙም፣ በስብሰባዎች ለይም አይሳተፉም፤
- እነዚህን ኮሚቴዎች ለመገምገም፤ እንደገና ለማደራጀት እና ለማጠናከር የሚያስችል መደበኛ መመሪያም የለም፤

## 2. የባለ ድርሻ አካላት አስተዳደር ስርዓት

በሁሉም የሰቆጣ ቃል ኪዳን ወረዳዎች ውስጥ ወጥነት ያለው አካሄድ እንዲኖር፣ የዚህን መመሪያ መገልገያ መሳርያዎች እና የአፈፃፀም ሂደቶችን በመጠቀም ባለድርሻ አካላት አስተዳደር እና የባለድርሻ አካላት ቅንጅት ስርዓቶችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡. እያንዳንዱ ወረዳ አሁን ያሉትን አሰራሮች እንዲገመግም እና አሰራሮቹን ከተቀመጠው የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካላት እና የወረዳ ስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ የስራ ዝርዝር አንጻር ማስተካከል ይጠበቅበታል፡፡.አተገባበሩም በመደበኛ ክትትልና ግምገማ ሂደት ውስጥ እንዲካተተ.ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የሚከተሉት አሰራሮች በወረዳዎችና በክልሎች እንዲተገበሩ ይመከራሉ፡፡.

1. የባለድርሻ አካላት የአሰራር ስርዓት በማድረግ አሁን ያለውን የባለድርሻ አካላት ቅንጅት እና የአጋር አካላትን አስተዳደር ሁኔታን መገምገም፡፡ የቅንጅት አሰራሩ ካልተፈጠረ መመሪያውን በመጠቀም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
2. .ቅንጅታዊ አሰራር በሚገኙበት ወረዳዎች ውስጥ በዚህ መመሪያ የሰፈሩትን ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ እንደገና ማሻሻልና ማስተከከል ያስፈልጋል፣
3. በዚህ መመሪያ የሚሰጡትን የውሳኔ ሃሳቦች ባገናዘበ መልኩ በእያንዳንዱ የቅንጅት አሠራር ላይ የሚሳተፉ የአባልነት ሁኔታ ማሻሻያ ይስፈልገዋል፣
4. የባለድርሻ አካላትን ቁመና ማሳያ መሳሪያ (stakeholders mapping tool) በመጠቀም በእያንዳንዱ ወረዳ ውስጥ በስርዓተ ምግብ ላይ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት በሙሉ መዘርዝር፣

5. የባለድርሻ አካላት ዝርዝርመላያ ቅጽ (stakeholder mapping)ትግበራን ማጠናቀቅ፣ ማለትም በስርዓት ምግብ እና በሰቆጣ ቃልኪዳን ግቦች ላይ በመመርኮዝ ጠቃሚና አስፈላጊ አጋሮችን ለይቶ ማወቅ፣
6. የቅንጅት አሰራሮችን እና የባለድርሻ አካላት አስተዳደር እንዴት እንደሚተገበር ተወያይቶ ስምምነት ላይ መድረስ፣
7. የአስተባባሪ አካሉን እና የቴክኒክ ኮሚቴውን ስብጥር በመወያየት መወሰን ይገባል፡፡ ሁሉም አግባብነት ያላቸው አባላት በእያንዳንዱ የቅንጅት አካል ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ፣ የአጋርነት እና የቅንጅት  የስብሰባ መረሃግብር ማዘጋጀት፣ የስራ ድረሻ እና እና ኃላፊነቶቻቸዉን ለይቶ ማሳወቅ፣ አጀንዳዎችን ማሳዎቅ፣ የአፈፃፀም እና የክትትል ሂደትን በመከታተል ዙሪያ መወያየትና መግባባት ላይ መድረስ፣
8. ሁሉንም ውሳኔዎችን በጥራት መመዝገብ፣ ለተወካዮች እና ለክልል የፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍል እንዲሁም ለክልል ፕሬዚዳንቶች በወቅቱ ማሳወቅ፣ እነዚህ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላቶች ጋር የመረጃ ልዉዉጥ መኖሩን  ማረጋገጥ፣

እንደ የአካባባው ሁኔታ ማስተካከል የሚችሉ ቢሆንም የወረዳ እና የክልል የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የቴክኒክ ኮሚቴ መደበኛ የስብሰባ ፕሮገራማቸውን በሚከተለው መንገድ እንዲያከናዉኑ ይመከራል

- የክልል የስርዓት ምግብ አስተባባሪ አካል (RNCB): በየሩብ ዓመቱ
- የክልል የስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ (RNTC): በየወሩ
- የዞን የስርዓት ምግብ አስተባባሪ አካል (ZNCB): በየሩብ ዓመቱ
- የዞን የስርዓት ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ (ZNTC): በየወሩ ዓመቱ
- የወረዳው የስርዓት ምግብ አስተባባሪ አካል (WNCB): በየወሩ
- የወረዳ የስርዓት ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ (WNTC):  በየወሩ

እያንዳንዱ ኮሚቴ መደበኛ የስብሰባ ቦታ፣ የስብሰባ ቀናትና ሰዓት እንዲኖሩት ይጠበቃል፡፡ መደበኛ ስብሰባዎች አስቀድሞ የታቀደ በእያንዳንዱ ወር ፣ ቀን እና ሰዓት የተወሰኑ መሆን አለባቸው ፡፡ ከወረዳዎች በተሰበሰበ አስተያየት መሠረት በወሩ መጨረሻ ቀናት (ከ 27 እስከ 29) በወረዳው አስተዳደር ጽ. ቤት አዳራሽ ከጧቱ 2.30 እስከ 5.00 ሰዓት ቢሆን መረጣል፡፡ ልዩ እና አስቸኳይ ስብሰባዎች በአካባቢዉ ሁኔታ እና በአብዛኛዎቹ የአባላት ፍላጎት መሠረት መከናወን አለበት ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ቀናትን በዞን እና በክልል ደረጃ ያሉ መዋቅሮችም ተግባራዊ ያደርጓቸዋል። በሁሉም ስብሰባዎች የሚመለከታቸዉ በየደረጃዉ ያሉ አስተባባሪ አካላት የማስተባበር፣ የመደገፍ እና

የተጠያቂነት እርምጃዎችን የመዉሰድ ሃላፊነት አለባቸዉ (ዝርዝር መረጃውን በአባሪ ክፍል ‹በ‹ ይመልከቱ) ፡፡.

## 2.1 የመመሪያው አተገባበር ስልት

**ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚከተሉት ሶስት ተመጋጋቢ የሆኑ ሦስት የትግበራ ሂደቶች ወይም ደረጃዎች አሉት፡**

**ደረጃ 1:- የዚህ መመሪያ የመጀመርያ ተግባር የመመሪያውን አጠቃላይ ሃሳብ እና በተቀመጡት የአሰራር ሂደቶች\ ስልት ላይ የጋራ መግባባት መኖሩን ማረጋገጥ ነው:: ሁሉም የሰቆጣ ቃል ኪዳን ሴክተር መስርያ ቤቶች እና ፈጻሚ አጋር አካላት (ሲቪክ ማህበራት፣ የእምነት ተቋማት እና የግል ሴክተሮች) ሁሉ እንዲጋበዙ እና በመመሪያው ላይ እንዲወያዩ ይጠበቃል፡፡ የወረዳው ስርዓተ ምግብ ተጠሪ ከወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ጋር በመተባበር ሂደቱን ያመቻቻሉ፣ አስፈላጊ ከሆነ ከክልል ፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍል /RPDU/ እና ከሙያዊ ድጋፍ ሰጪወች /TA/ እገዛ ይጠይቃሉ፡፡**

**ደረጃ 2፡- የወረዳውን የስርዓተ ምግብ የቅንጅት አሰራር ሁኔታ የመገምገምና እንዲሁም በተቀመጠው መመዘኛ መስፈርት መሰረት ደረጃ ይሠጣል፡፡ (በአባሪ H ውስጥ ያለውን የምዘና ስርዓት ይመልከቱ)**

**ደረጃ 3: ግምገማው ላይ ተመስርቶ የተቀናጀ አሰራርን እንደገና ማሻሻል እና በሚወሰዱ እርምጃዎች ላይ የጋራ ስምምነት መድረስ፣ ከሚደረገው ግምገማ እና ከሚሰጠው ውጤት በመነሳት ሊወሰዱ የሚችሉት የመፈተሄ ሃሳቦች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ፡-**

- **አሁን ያለውን የቅንጅት አሰራርን ከተወሰነ ማሻሻያ ጋር ማስተካከል (ለምሳሌ አንድ ወይም ሁለት አባላትን በመጨመር)፣**
- **ያለውን የቅንጅት አሰራር ዘዴን ዋና ዋና በሚባሉ ማሻሻያዎች እንደገና ማስተካከልና ማደስ (ለምሳሌ የጎደለውን ክፍተት በመሙላት)፣**
- **በግምገማው በተገኘው ውጤት መሰረት ውጤታማ ያልሆነውን የቅንጅት አሰራር ማስተካከልና የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካሉንና የወረዳ ስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴውን እንደገና ማቋቋም እና በተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ፣**
- **እነዚህ ኮሚቴዎች ባልተቋቋሙበት አካባቢ አዲስ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካልና የወረዳ ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ ማቋቋም/መመስረት፣**

**በወረዳ ደረጃ አስተባባሪ አካላትን ማቋቋም/መልሶ ማደራጀት**

እያንዳንዱ ወረዳ የሰቆጣ ቃልኪዳን /ሁለተኛውን የብሄራዊ ስርዓተ ምግብ ፕሮግራም/ ኮሚቴውን በማስተካከልና በማደራጀት የወረደ ስርዓተ ምግብ ፕሮግራም አስተባባሪ አካል ማቋቋም እና እንደዚህ አይነቱን የቅንጅት/የትብብር/ አሰራር በግምገማው ወቅት አለመኖሩ ከታወቀ ፈጥኖ መመስረት ያስፈልጋል፡፡ ለዉጤታማ የባለድርሻ አካላት ትብብር እና ለአጋር አካላት አስተዳደር ከክልል እስከ ወረዳ ባሉ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ በሚከተለው የቅንጅት ስልት መሰረት መቋቋም ይኖርበታል

**የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል (WNCB)**

የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል በወረዳው ውስጥ የሚከናወኑ ሁሉንም የስርዓተ ምግብ ስራዎችን የማሳለጥ እና የማስተባብር ሃላፊነት ያለው ኮሚቴ ነው፡፡ የወረዳ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ለተወሰኑ የፕሮጀክት ስራዎች የተቋቋመ አካል አይደለም፡፡ ይልቁንም የብዙ ባለድርሻ አካላት ትብብር እና ባለድርሻ አካላት የአሰራር ስርዓት ነው፡፡ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ለሰቆጣ ቃልኪዳን *መመሪያዎችን*፣ ስልታዊ ዕቅዶች እና የስርዓተ ምግብ ፕሮግራሞች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት በሁሉም የስርዓተ ምግብ ተግባራት ላይ ክትትል እንዲያደርግ ይጠበቅበታል፡፡ (*በአባሪ A የተመለከተውን የWNCB የስራ ዝርዝር ቢጋር ይመልከቱ)፡፡* የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አካሉን ወደስራ የማስገባትና የማስጀመር ወይም ከሀገራዊ የስርዓተ ምግብ ስርዓቱ ጋር ለመጣጣም ያለውን የጋራ ማስተባበሪያ ዘዴ እንደገና የማደረጀት ወይም መልሶ የማቋቋም ስራ እንዲያከናውን ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ወረዳ ዋና አስተዳዳሪው የተስተካከለውን *መመሪያ* መከተል እና በዚህ *መመሪያ* ውስጥ እንደተገለጸው የወረዳ ስርዓተ ምግብ አካል የስራ ዝርዝር ቢጋር (TOR) ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ (በዓባሪ A *የተመለከተውን* የስራ ዝርዝርውል ይመልከቱ).

**የወረዳው ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ (WNTC)**

የወረዳ ስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ ለወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ሙያዊ አጋዥ ሃይል ሲሆን በወረዳ ውስጥ ላሉ ሴክተር መስርያ ቤቶች እና መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አጋር አካላት የሥርዓተ ምግብ ተግባር የማቀድ፣ የመተግበር እና የመከታተል ሃላፊነት አለዉ፡፡ የወረዳው ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ በዋናነት በአተገባበር ቁጥጥር፣ በፕሮግራም ልማት (program development) ፣ አዲስ የፕሮጀክት ረቂቅ ማዘጋጀትና መገምገም (proposal reviewɷ) እና ሙያዊ እገዛ በመስጠት ላይ ያተኩራል፡፡ ይህ ኮሚቴ

እንደገና ሊደራጅ ወይም በአዲስ መልክ ሊቋቋም የሚችል ሲሆን የሚያካትታቸውም የእያንዳንዱን የሰቆጣ ቃልኪዳን የመንግስት መስሪያ ቤቶች የስርዓተ ምግብ ተጠሪ ወይም ባለሞያና የስነምግብ ኤክስፐርት፣ የፕሪጀክት አስተባባሪዎችን፣ የትግበራ አጋሮችን እና መሰል ፕሮጀክት ያላቸውን ሲቪክ ማህበራትን ወይም ወኪሎቻቸውን ነው፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ተነሳሽነቱ ከወረዳው የስርዓተ ምግብ ተጠሪወች መምጣት አለበት፡፡

**አቅም ግንባታ**

### 2.1.1 የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል (WNCB) ስብጥር

እያንዳንዱ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የወረዳ ስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ (WNTC) ከኮሚቴው አባላት የተመረጡ የራሳቸው ሊቀመንበር እና ፀሀፊ ይኖሩታል፡፡ መንግስት በፌዴራል ደረጃ የብሄራዊ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና ብሔራዊ የስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ  በተሸለ ሁኔታ ተቋቁሟል፡፡ የብሄራዊ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የቢሄራዊ ስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ የአባላት ስብስብ በብሄራዊ ስርዓተ ምግብ ፕሮግራም (NNP) በተጠቀሰዉ መሰረት ይሆናል፡፡ የስርዓተ ምግብ ፕሮግራሙን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ እነዚህን የቅንጅት ስልቶች በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ በተመሳሳይ መልኩ ይተገበራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የወረዳ ስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ የአባልነት ስብጥር በሚመለከታቸው አካላት በሚዘጋጁ መመሪያዎች መሰረት ይሆናል፡፡ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ለዞን ስርዓተ ምግብ አስተባበሪ አካል ፣ የዞን ስርዓተ ምግብ አስተባበሪ አካል ለክልል ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡ የክልል ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ለብሄራዊ ሰርዓተ ምግብ አስተባባሪ (NNCB) ሪፖርት ያቀርባል፡፡ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚያተኩረው በአመራር፣ በፖሊሲ፣ በአስተዳደር፣ በሃብት አጠቃቀም፣ አጋርነትን ማስተባበር እና በፕሮግራም ክለሳ ላይ ነው፡፡

የወረዳው ስርዓተ ምግብ አካላት ስብጥር በተቋማዊ ውክልና ላይ የሚመሰረቱ እንደመሆናቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የሴክተር ኃላፊዎች ወይም ተወካዮች የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ዋነኛ አባላት ይሆናሉ፡፡

| ተ/ቁ | የተቋሙ ስም | በተቋሙ ያለው ሃላፊነት | በኮሚቴው ውስጥ |
|---|---|---|---|

| | | | የሚኖራቸ ው ሚና |
|---|---|---|---|
| 1 | ወረዳ አስተዳደር | ዋና አስተዳዳሪ | ሊቀ መንበር |
| 2 | ወረዳ ጤና ጽ/ቤት | ጽ/ቤት ሃላፊ | ጸሃፊ |
| 3 | ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት | ጽ/ቤት ሃላፊ | አባል |
| 4 | ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት | ጽ/ቤት ሃላፊ | ፀሓፊ |
| 5 | ወረዳ እንስሳት እና አሳ ሃብት ልማት ተጠሪ ጽ /ቤት | ጽ/ቤት ሃላፊ | አባል |
| 6 | ወረዳ ውሃ፣ መስኖ እና ኢነርጂ ጽ/ቤት | ጽ/ቤት ሃላፊ | አባል |
| 7 | ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት | ጽ/ቤት ሃላፊ | አባል |
| 8 | ወረዳ ሴቶች እና ህጻናት ጉዳይ ጽ/ቤት | ጽ/ቤት ሃላፊ | አባል |
| 9 | ወረዳ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር | ጽ/ቤት ሃላፊ | አባል |
| 10 | ወረዳ መንገድ እና ትራንስፖረት ጽ/ቤት | ጽ/ቤት ሃላፊ | አባል |
| 11 | የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንተርፕራይዝ ልማት | ጽ/ቤት ሃላፊ | አባል |
| 12 | ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ወይም የስራ ሂደት | ጽ/ቤት ሃላፊ ወይም የስራ ሂደት ሓላፊ | አባል |
| 13 | ዋና ዋና ተፅኖ ፈጻሚ አጋር አካላት (Lead IPs) | ተወካይ /ፕሮጀክት ማኔጀር/ | አባል |
| 14 | ዋና ዋና ሲቪክ ማህበር ድርጅቶች (Lead CSOs) የሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች | ሃላፊ | አባል |
| 15 | የ ከፍተኛ ት/ት ተቋማት (ዩኒቨርሰቲ) እና የጥናትና ምርምር ተቋማት | ተወካይ | አባል |
| 16 | የወረዳው ህዝብ ግንኙነትና ኮምኒኬሽን | ሓላፊ | አባል |

የወረዳው ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል (WNCB) በወረዳ ዋና አስተዳዳሪው መመራት ያለበት ሲሆን ፣ፀሃፊው ደግሞ የወረዳዉ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ወይም የወረዳው ግብርና ፅሕፈት ቤት ሃላፊ ይሆናል፡፡ የወረዳው ስርዓተ ምግብ አካል (WNCB) በቅንጅት ስልቶች የመጀመርያ የትግበራ ደረጃ እና በአባላት ምክክር መሰረት ሊቀየር ይችላል፡፡

### 2.1.2 የወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ ስብጥር

የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ ስብጥር ከሰቆጣ ቃል ኪዳን ጽ/ቤቶች እና በስርዓተ ምግብ ዙሪያ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ያካተተ ይሆናል ፡፡ የኮሚቴው አባል ባለድርሻ አካላት (ከመንግስት ሴክተር መስርያ ቤቶች ዉጭ የሆኑ) ስብጥር ከወረዳ ወረዳ የሚለያይበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ በዋናነት ግን ተቋማት የሚኖራቸው ውክልና በስርዓተ ምግብ ዙሪያ ባላቸው እውቀትና ክህሎት፣ በሚያከናውኑት የጤና ተግባራት፣ በፕሮግራም ዝግጅትና ትግበራ፣ እንዲሁም በክትትልና ግምገማ እና በመሳሰሉት አስተዋፆ ይሆናል፡፡ የኮሚቴው የተቋማት ውክልና በየጊዜው በሚኖሩ ውይይቶቸ የሚሻሻል ይሆናል፡፡

| ተ/ቁ | የተቋሙ ስም | በኮሚቴው ውስጥ የሚኖራቸው ሚና |
|---|---|---|
| 1 | ወረዳ ጤና ጽ/ቤት ወይም ግብርና ፅሕፈት ቤት | ሰብሳቢ |
| 2 | የወረዳ አስተዳደሩ ሰቆጣ ቃል ኪዳን (ስርዓተ ምግብ ተጠሪ) ተወካይ | ፀሃፊ |
| 3 | ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ስርዓተ ምግብ ተጠሪ | አባል |
| 4 | ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ስርዓተ ምግብ ተጠሪ | አባል |
| 5 | ወረዳ እንስሳት እና አሳ ሃብትልማት ጽ /ቤት ስርዓተ ምግብ ተጠሪ | አባል |
| 6 | ወረዳ ውሃ፣ መስኖ እና ኢነርጂ ጽ/ቤት ስርዓተ ምግብ ተጠሪ | አባል |
| 7 | ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ስርዓተ ምግብ ተጠሪ | አባል |
| 8 | ወረዳ ሴቶች እና ህጻናት ጉዳይ ጽ/ቤት ስርዓተ ምግብ ተጠሪ | አባል |
| 9 | ወረዳ ሰራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ተወካይ ስርዓተ ምግብ ተጠሪ | አባል |
| 10 | ወረዳ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ተጠሪ | አባል |

| | | |
|---|---|---|
| 11 | ወረዳ መንገድ እና ትራንስፖረት ጽ/ቤት ተጠሪ | አባል |
| 12 | የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንተርፕራይዝ ልማት ተጠሪ | አባል |
| 13 | ዋና ፈጻሚ አጋር አካላት(Lead IPs) ስርዓተ ምግብ ተጠሪ | አባል |
| 14 | የከፍተኛ ት.ት ተቋማት (ዩኒቨርሰቲ) እና የጥናትና ምርምር ተቋማት ተጠሪ | አባል |
| 15 | የወረዳው ይህዝብ ግንኙነትና ኮምኒኬሽን | አባል |

**የወረዳዉ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ የስብሰባ አካሄድ/ አደረጃጀት**

የክልል ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የክልል ስርዓተምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የሰቆጣ ቃልኪዳን ፈፃሚ አካላትን የፕሮግራም አፈፃፀም እና የመረጃ አያያዝ በተመለከተ የስብሰባ እና የግምገማ ስርዓትን በየሩብ አመቱ የሚያካሂድ ይሆናል፡፡ የወረዳ ስርዓተምግብ አስተባባሪ አካል መደበኛ ስብሰባ በየወሩ እንዲካሂድ የታሰበ ሲሆን የወረዳ ስርዓተምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ በየወሩ እንዲሰበሰቡ በእቅድ ተይዟል፡፡ የስብሰባዎቹ ብዛት (ድግግሞሽ) መጠን በባለድርሻ አካላት የመጀመርያ የትግበራ ምዕራፍ ወቅት የሚሞክር ሲሆን ከወረዳወች በሚገኝ ግብረመልስ የሚሻሻል ይሆናል፡፡ የዞን ስርዓተምግብ አስተባባሪ አካል እና ስርዓተምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ የቅንጅት ሁኔታ እንደአሰፈላጊነቱ በክልሉ አማካኝነት በተመሳሳይ የተቋማት አደረጃጀት መሰረት የሚቋቋም ይሆናል፡፡

**የኮሚቴዉ የስብሰባ አደረጃጀት**

**የስብሰባ ቦታ፡** የወረዳዉ አስተዳደር ጽ/ቤት የስብሰባ ቦታ እንዲሆን ይመከራል፡፡ ነገርግን ኮሚቴው ቋሚ የሆነ የመሰብሰበያ ቦታ መምረጥ እና መወሰን ይችላል፡፡ በቅንጅት ከሚሰሩ አጋር አካላት ወይም ሲቪክ ማህበራት ቢሮ ዉስጥ የኮሚቴዉ ቋሚ የስብሰባ ቦታ ባይሆን ይመረጣል፡፡ **የሻሂ ቡና ወጭ፡** አጋር አካላት እና በየደረጃዉ ያሉ የወረዳዉ አስተዳደር አካላት ለኮሚቴው ስብሰባወች እና የሻሂ ቡና ወጭ ለመሸፈን የሚዉል የአካባቢዉን ዋጋ መሰረት ያደረገና የፋይናንስ መመርያን ባገናዘበ መልኩ በጀት ይመደባሉ፡፡ የወረዳ ስርዓተምግብ አስተባባሪ አካል ይህን በጀት መመደቡንና አጠቃቀምን በተመለከተ ከወረዳ ስርዓተምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በሚኖረዉ የጋራ ስብሰባ ወቅት ይከታተላል (ያረጋግጣል)፡ ፡

**የስብሰባ መርሃግብር፡**

1. <u>የወረዳዉ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል፡</u> የወረዳዉ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል መደበኛ ስብሰባ በየወሩ መጨረሻ ቀናት ለማካሄድ የታሰበ ሲሆን አስቸኳይ ወይንም ልዩ ስብሰባዎች በማንኛዉም ጊዜ ሊጠሩ ይችላሉ፡፡
2. <u>የወረዳዉ ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ፡</u> የቴክኒክ ኮሚቴዉ ስብሰባ የሚያተኩረዉ ተግባራትን ለመከታተል እና በታቀዱ ፕሮግራሞች ላይ ሙያዊ ግምገማ ለማካሄድ ስለሆነ በወር አንድ ጊዜ በአባላት በተመረጠ የስብሰባ ቀን ይካሄዳል፡፡ ረቂቅ አጀንዳ ለማዘጋጀት እና ሙያዊ ድጋፍ ለመሰጠት ይረዳ ዘንድ የወረዳዉ የቴክኒክ ኮሚቴ የስብሰባ ቀናት የወረዳዉ አስተባባሪ አካል ከመሰብሰቡ በፊት ቢሆን ይመረጣል፡፡
3. <u>የዞን ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የቴክኒክ ኮሚቴ፡</u>
   እስካሁን ባለዉ የመንግስት አደረጃጀት መሰረት በዞን ደረጃ የማስተባበሪያና የቴክኒክ ኮሚቴዎች ሰላልተቋቋሙ ይህ መመሪያ ለዞን ኮሚቴዎች የማጣቀሻ ውሎችን አይጨምርም ፡፡ ሆኖም መንግስት የዞን ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የዞን ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ በዞን ደረጃ ከተመሰረተ በክልል ደረጃ የተጠቀሱትን አባሪወች ከዞን ሁኔታዎች ጋር በማስማማት መጠቀም ይቻላል፡፡ ኮሚቴዎች በማን ሰብሳቢነት እንደሚመሩ በዞን አስተዳዳሪዉ የሚወሰን ይሆናል፡፡
4. <u>የክልል ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የቴክኒክ ኮሚቴ፡</u> በክልል ደረጃ ያሉ አስተባባሪ አካላት እና የቴክኒክ ኮሚቴ  በሩብ አመት አንዴ ይሰበሰባሉ፡፡ የክልሉ አስተባባሪ አካል ስብሰባ የቴክኒክ ኮሚቴዉን ስብሰባ ተከትሎ የሚካሄድ ሲሆን ለዉሳኔ ሰጭወች የሚሆኑ የመፍትሄ ሃሳቦችን እና የፖሊሲ ጉዳዮችን ግምት ዉስጥ ያስገባ ይሆናል፡፡

<u>የስብሰባ አጀንዳ፡</u> የእያንዳንዱ ስብሰባ አጀንዳወች የኮሚቴዉን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሃፊ በማማከር በወረዳዉ ስራተ ምግብ ፎካል ፐርሰን አማካኝነት በረቂቅ መልክ እንዲያዘጋጅ ይደረጋል፡፡ በክልል ደረጃ የስርዓተ ምግብ ተጠሪ የክልሉን ርዕሰ መስተዳድር እና የፕሮግራም  ማስፈፀምያ ክፍል በማማከር የስብሰባ አጀንዳወችን ያዘጋጃል፡፡ ረቂቅ የስብሰባ አጀንዳወች በፀሃፊዉ አማካኝነት ለሁሉም የኮሚቴ አባላት ከስብሰባዉ ቀን አንድ ሳምነት አስቀደሞ ለግብዓት እና እዉቅና ያመች ዘንድ የስብሰባ ቀን እና ቦታ በማስታወስ በኤሌክተሮኒክስ መልክት፣ በጹሁፍ መልክት ወይንም በደብዳቤ በመጠቀም መልዕክት ያስተላልፋል፡፡

በእያንዳንዱ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል የስብሰባ አጀንዳወች ዝርዝር ዉስጥ ሊካተቱ የሚገቡ ሃሳቦች

- ከባለፈዉ ስብሰባ የተላለፉ ዉሳኔወች የአፈጻጸም ሁኔታ ክትትልን በተመለከተ፣
- ከቴክኒክ ኮሚቴዉ እና ከእያንዳንዱ ጽ/ቤቶች የተገኙ ጥቆማወች እና አዳዲስ ሃሳቦች፣
- በእያንዳንዱ ጽ/ቤቶች በእቅድ የተቀመጡ ተግባራትን ለማሰፈፀም ያጋጠሙ ችግሮች እና ተግዳሮቶች፣
- በእያንዳንዱ ጽ/ቤቶች ስር ያሉ ስርዓተምግብ ነክ ፕሮጀክቶች የበጀት አጠቃቀም፣
- የሃብት ማሰባሰብ እና የፋይናንስ መረጃወችን ለመተንተን የምንጠቀምበትን መገልገያ ቅፅ ማሻሻል (Resource Tracking And Financial Analysis Tool)፣
- የባለድሻ አካላት ዝርዝር ማሳያ መገልገያ ቅፅ (Stakeholders' Mapping Tool) ማሻሻያ ሃሳቦች፣
- ከወረዳዉ ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ የተቀመጡ የመፍትሄ ሃሳቦች ማጠቃለያ፣

<u>የስብሰባ የቆይታ ጊዜ፡</u> የእያንዳንዱ ስብሰባ የቆይታ ጊዜ በስብሰባ አጀንዳወች የሚወሰን ቢሆንም ዉይይቱን ለማስኬድ እና መረጃወችን ለመለዋወጥ በቂ መሆን ይኖርበታል፡፡ የስብሰባ ሰዓት አስቀድሞ የሚወሰን እና ለተሳታፊወች መልዕክቱ የሚተላለፍ ሆኖ በእቅድ በመመራት ሁሉንም አሳታፊ መሆን ይኖርበታል፡፡ የስብሰባ ቆይታ በቀን ከሶስት (3) ሰዓት በላይ ባይሆን ይመከራል፡፡ <u>የመረጃ አያያዝ፡</u> ሁሉም ስብሰባወች በቃለጉባዔ መዝገብ (በ አባሪ ..በተጠቀሰዉ) መሰረት ሊመዘገቡ ይገባል፡፡ ሌላ ተመራጭ የአመዘጋገብ ስልት ካለ በወረዳ አስተዳደሩ የሚወሰን ሆኖ ሁሉም መዝገቦች በቀላሉ እንዲገኙ እና ስራ ላይ እንዲዉሉ በተመረጠ አንድ ቦታ ላይ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ የኦንላይን አጋር አካላት ማስተባበር ስርአት ተግባራዊ ከተደረገ በኤሌክትሮኒክስ ሰለሚሞላ ሁሉም አባላት፣ የክልል አስፈጻሚ አካላት እና የክልልና የፌደራል የፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍል በቀላሉ ሊያገኟቸዉ እና ሊጠቀሙባቸዉ ይችላል፡፡ ሁሉም የቃለጉባዔ መዝገቦች ከስብሰባዉ በኋላ ባሉ አንድ ሳምንት ቀናቶች ዉስጥ ሊፈረሙ እና ለሚሉ ይገባል፡፡ በቅንጅት የተዘጋጀ የስርዓተ ምግብ ዕቅድ፣ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እቅዶች፣ መደበኛ ሪፖርቶች እና ቃለ ጉባዔ መዝገቦች የሚቀመጡበት ቢያንስ አንድ ማህደር በአስተዳደር ጽ/ቤት ሊዘጋጅ ይገባል፡፡

**የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል የስራ ድረሻ እና ሃላፊነቶች**

የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና የወረዳ ስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ የስራ ድረሻ እና ሃላፊነቶችን ያካተተ የስራ ዝርዝር (ቢ.ጋር) እንደቅደም ተከተላቸዉ በአባሪ 1 እና 2 ተካቷል፡፡

**የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ሰብሳቢ**

የወረዳዉ ዋና አስተዳዳሪ የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ሰብሳቢ ይሆናል፡፡ በዋናነትም አስተባባሪ ኮሚቴዉን የመምራት፣ ኮሚቴዉን ወክሎ የመገኘት፣ እና የወረዳዉ ስርዓተ ምግብ (ተጠሪ) በመሆን የማገልገል ሃላፊነት አለበት፡፡

**የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ፀሃፊ**

የወረዳዉ ጤና ጽ/ቤት ሓላፊ ወይም ግብርና ፅሕፈት ቤት ሓላፊ የስርዓተ ምግብ የአስተባባሪ አካል ፀሃፊ በመሆን ይሰራል፡፡ ፀሃፊዉ በብቃት/ሜሪት የሚመደብ የሆናል፡፡ የአስተባባሪ ኮሚቴዉን የስብሰባ ቃለ ጉባዔ መመዝገብ፣ የኮሚቴዉ ሰብሳቢ በለሉበት ተክቶ የመስራት እና ሌሎች የኮሚቴዉ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የመከታተል ሃላፊነት አለበት፡፡ የኮሚቴውን የስብሰባ ቃለ ጉባኤ እና ሌሎች ሰነዶችን መፈረማቸውን ይከታተላል በአገባቡ ይይዛል፡፡

**የወረዳ ስርዓተ ምግብ \ ሰቆጣ ቃልኪዳን ተጠሪ የስራ ድርሻና ሓላፊ**

- ለወረዳዉ የቴክኒክ ኮሚቴ መደበኛ የስብሰባ አጀንዳዎችን በማርቀቅ ለኮሚቴዉ ፀሃፊ ከስብሰባዉ ቀን ከአንድ ሳምነተ በፊት በማቅረብ የኮሚቴዉ አባላት አስተያየት እና ድጋፋቸዉን እንዲሰጡበት ማድረግ፣
- የሚተገበሩ ክንዉኖችን በመለየት ለሚመለከታቸዉ ጽ/ቤቶች እና አጋር አካላት መረጃዉን በወቅቱ ማስተላለፍ፣
- የስብሰባ ቃለጉባዔ መዝገብን እና በሚከናወኑ ተግባራት ላይ አስተያየት እንዲሰጡበትና ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ለአባላት ማቅረብ፣
- የወረዳዉ ሰቆጣ ቃልኪዳን ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ መሳተፍ እና ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣
- ወረዳዉን በመወከል ከክልሉ የፕሮግራም ማስፈጸሚያ ክፍል ጋር መረጃ መለዋወጥ ፣
- አጋር አካላት እና የሰቆጣ ቃል ኪዳን ጽ/ቤቶች በእቅድ የተቀመጡ ተግባራት እንዲፈፀሙ እና መረጃ መለዋወጫ ሰነዶች ለሚመለከተዉ አካል እንዲያቀርቡ ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ማስታወስ፣

- የባለድርሻ አካላት ትብብር  መከታተያ ዝርዝረ መከታተያ ቅፅ በየጊዜዉ መሻሻሉን (መከለሱን) ማረጋገጥ፣
- ለሃብት ማሰባሰብ እና ለፋይናንስ መረጃወች መተንተኛ የምንጠቀምበት መሳርያ በተገቢዉ መልኩ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፣
- ከእያንዳንዱ የአገልግሎት ማሳለጫ ቅፅ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን ለተጠቃሚወች ግልፅ ማድረግ፡፡ ለምሳሌ የባለድርሻ አካላት ጥምረት ወይም ትብብር ማብራራት፣ ባለድርሻ አካላት ያሉበት ሁኔታ ማሳያ እና የፋናንስ መረጃወች መግለጫ/ ማሳያ ለወረዳዉ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ ኣካል እና  አካል ሰብሳቢ ግንዛቤ መፈጠር፣
- ወርሃዊ እና የሩብ አመት እቅዶች እንዲዘጋጁና የአፈፃፀም ግምገማ እንዲካሄድ በበላይነት መምራት፣
- የድጋፍ ጉብኝቶችን እና የመስክ ጉዞወችን በማዘጋጀት በወረዳ ስርአተ ምግብ አስተባባሪ አባላት መካከል የመረጃ ልዉዉጥ እንዲኖር ማድረግ፣
- ለቀጣዩ የወረዳ ሰርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል የስብሰባ አጀንዳዉችን ማዘጋጀት፣

### 2.2 በክልል ደረጃ የዘርፈብዙ ባለድረሻ አካላት ቅንጅት እና አጋር አካላትን ትብብር

የክልሉን የሴክተሮች ቅንጅት ለመከታተል አና አጋር አካላትን ለማስተባበር በተመሳሳይ መልኩ ይህን የአሰራር መመርያ፣ የባለድረሻ አካላት መከታተያ ቅፅ መተግበርያ መሳርያ (stakeholder mapping tool) የተጠያቂነት መከታተያ (accountability tool) ፣ ሌሎች መመርያዎች (guidelines) እና የባለድረሻ አካላት አፈፃፀም ትንተና ጥቅም ላይ ይዉላል፡፡ የባለድረሻ አካላት ቅንጅት ማስተባበርያ መከታተያ ቅፅ የክልሉን የባለድረሻ አካላት ቅንጅት መከታተያ ቅፅ፣ የባለድረሻ አካላትን አፈፃፀም መገምገም እና የተጠያቂነት መከታተያ ቅፅ መጠቀም ይቻላል፡፡

የወረዳወች የአፈፃፀም ደረጃ፣ የሃብት አጠቃቀም እና የሰቆጣ ቃል ኪዳን አካላት ቅንጅት ያለበት ሁኔታ በክልል ደረጃ ይገመገማል፡፡ በክልል ደረጃ የሚዘጋጀዉ ይህ ሁሉን አሳታፊ የቅንጅት ስብሰባ በየሩብ አመቱ ለማካሄድ በእቅድ የተያዘ ሲሆን የክልል ቢሮዎች፣ ለጋሽ ድጅቶች፣ የክልሉ የፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍል እና ለተግባሩ የሚረባረቡ አጋር አካላት የሚሳተፉበት ይሆናል፡፡ የክልሉ ስርዓተምግብ አስተባባሪ አካል ዝርዝር የስራ ድርሻ ወይንም ቢ.ጋር በአባሪ ሐ ተጠቅሷል፡፡

### 2.2.1. የክልሉ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል የአባላት ስብጥር እና ሃላፊነት

የክልሉ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል  ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በአባልነት የያዘ ይሆናል

- የክልል አስተዳደር ቢሮ (የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር) - የክልሉ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ሰብሳቢ
- የክልል ጤና ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የክልል ግብርና ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የክልል እንስሳት እና አሳ ሃብት ልማት ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የክልል የዉሃ፣ መስኖ እና ኢነርጅ ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የክልል የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የክልል የሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የክልል የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የክልል አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የክልል መንገድ እና ትራንስፖርት ቢሮ- ሃላፊ/ ምክትል
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሰቲ) እና የጥናትና ምርምር ተቋማት ተጠሪ
- የክልል የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች- ሃላፊ/ አስተባባሪ/ ተወካይ
- የሀይማኖት ተቋማት ተወካይ

**የስራ ድረሻ እና ሃላፊነት**

- በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ የስርዓተ ምግብ ፕሮግራሞች አጠቃላይ አመራር ይሰጣል፡፡
- የወረዳወችን የአፈፃፀም ሪፖርት ይገመግማል ፡፡
- የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን፣ ለጋሽ ደርጅቶችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና የግል አጋሮችን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ባለድርሻ አካላትን ማስተባበር፣ መምራት እና ማመቻቸት፡፡
- በሃብት ትንተና መረጃ ዘገባ (ሪፖርት) ላይ የስርዓተ ምግብ ሀብት ምደባን  አንዱ የክትትል ስርዓት አድርጎ መጠቀም።
- የወረዳውን የሰቆጣ ቃልኪዳን  ስትራቴጂካዊ ግቦች ለመደገፍ ሃብቶችን ማሰባሰብ እና የሃብት አጠቃቀምን መከታተል፡
- የአተገባበር ሁኔታን፣ ባለድርሻ አካላት  የትብብር ሁኔታ ማሳያ ዳሽቦርድን፣ በተለይም ከሰቆጣ ቃልኪዳን  ጋር የተገናኙ ስትራቴጂካል ዓላማዎችን እና ግቦችን መገምገም።
- ዋና የትግበራት አፈፃፀም ደረጃወችን መገምገምና ፈታኝ ሁኔታዎችን መፍታት፡፡

- በአጋር ድርጅቶች መካከል ቅንጅት እና ትብብርን እንዲኖር ማመቻቸት፡፡
- የአጋር ድርጅቶችን የአፈፃፀም ሪፖርት ወደ ወረዳ በወቅቱ እንዲያስረክቡ ማመቻቸት ፡፡
- የስርዓተ ምግብ ጉዳዮችን በወረዳ ልዩልዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ጠንካራ ግንኙነት መፍጠር
- ለሰቆጣ ቃልኪዳን ትግበራ የሚረዱ ስትራቴጂወችን መንደፍ እና እቅድ ማዘጋጀት፡፡
- የስርዓተ ምግብ በተለይም የሰቆጣ ቃል ኪዳን ለባለብዙ ባለድርሻ አካላት ቅንጅት ውጤታማነት መገምገም ፡፡
- ዓመታዊ እና የግማሽ ዓመት ሪፖርቶችን እንዲሁም በጀቶችን መገምገምና ማጽደቅ፡፡

**የክልሉ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ሰብሳቢ**

የክልሉ ር/መስተዳድር የክልሉ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ሰብሳቢ ይሆናል፡፡ በእቅድ የተቀመጡ ተግባራት እንዲሳኩ አመራር የመስጠት እና ስብሰባወችን የመምራት ሃላፊነት አለበት፡፡

**የክልሉ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ፀሃፊ**

የፀሃፊዉ የስራ ድርሻ (ሃላፊነት) በዋናነት የኮሚቴ ስብሰባዎችን መመዝገብ፣ የኮሚቴዉ ሰብሳቢ በማይገኙበት ጊዜ እሳቸዉን ተክተዉ የመምራት፣ እና ሌሎች የኮሚቴ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ማከናወንን ይመለከታል፡፡

### 2.2.2. የክልሉ የስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ ስብጥር፣ የስራድረሻ እና ኃላፊነት

የክልሉ የስርዓተ ምግብ  የቴክኒክ ኮሚቴ የሚከተሉትን አባላትን ይይዛል ፡፡

- የክልል ጤና ቢሮ ወይም ግብርና ቢሮ- ተወካይ
- የክልል ጤና ቢሮ ግብርና ቢሮ- ተወካይ
- የክልሉ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ክፍል ሃላፊ ፀሓፊ
- የክልል እንስሳት እና አሳ ሃብት ልማት ቢሮ- ተወካይ
- የክልል የዉሃ፣ መስኖ እና ኢነርጅ ቢሮ- ተወካይ
- የክልል የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ- ተወካይ
- የክልል የሴቶች እና ህፃናት ጉዳይ ቢሮ- ተወካይ
- የክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ- ተወካይ
- የክልል የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ- ተወካይ
- የክልል አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ቢሮ- ተወካይ

- የክልል መንገድ እና ትራንስፖረት ቢሮ- ተወካይ
- የከፍተኛ ትመህርት ተቋማት (ዩኒቨርሰቲ) እና የጥናትና ምርምር ተቋማት ተወካይ
- የክልል የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች- ተወካይ

የክልሉ የስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ የስራ ድረሻዎች እና ሃላፊነቶች (በተጨማሪነት በአባሪ ›ሡ› ይመልከቱ)

### 3. ቅንጅዊ አሰራርን ለመምራት የምንጠቀምባቸው አሰራሮችና መተግበርያ መሳርያዎች

ባለድርሻ አካላት በአግባቡ ለመምራት ልዩ ልዩ  አሰራሮችን መተግበር የሚጠይቅ ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ሲሆኑ ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በአባሪ ክፍሉ ተቀምጠዋል

- የኮሚቴዎች እና አመራሮች የስራ ዝርዝር (ቢ.ጋር)
- የመወያያ አጀነዳ ዝግጅት
- የባለድረሻ አካላት የመከታተያ ቅፅ Stakeholder mapping tool
- የሃብት ምደባ ክትትልና ትንተና ቅፅ Resource tracking tool
- ቃለ ጉባዔ ዝግጅት
- የስብሰባ ቃለጉባኢ ለሚመለከታቸው ማጋራት

ከዚህም ባሻገር የሃብት አጠቃቀም ዝርዝር መረጃ፤ ባለድርሻ አካላት የአፈፃጸም ግምገማ፤ የቅንጅት አሰራር ሁኔታን እና የሃብት አጠቃቀምን የሚሳይ የመረጃ ቋት መሰረት አድጎ መወያት ጠቃሚ ይሆናል፡፡ የባለድርሻ አካላት አፈፃጸምና የቅንጅዊ አሰራርን ለመገምገም ተገቢዉን የክትትልና ግምገማ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡

**የዘረፈ ብዙ ሴክተሮችና አጋር ድርጅቶች ቅንጅትን ለመከታተል የምንጠቀምባቸው አሰራሮች**

ይህ ክፍል ከሁለተኛዉ ዙር ብሄራዊ የስርዓተ ምግብ ፕሮገራም ምዕራፍ 6 እና ከሰቆጣ ቃልኪዳን የመጀመሪያ የሙከራ ትግባራ (2009-2012) የኢንቨስትመንት እቅድ ክፍል 8 ጋር ግንኙነት አለዉ፡፡ ትኩረት የሚያደርገዉም ቃል ከዳኑ በሚተገብርባቸው የዘርፈ ብዙ ሴክተሮች አጋርነት እና ቅንጅትን ለመምራት የቁጥጥር ስርዓቱን ዉጤታማነት ለማሳየት ነዉ፡፡

**የባለድርሻ አካላት አጋርነት እና ቅንጅት ዉጤታማነት መገምገም**

በዚህ ክፍል በክልል እና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የዘርፈ ብዙ ሴክተሮችን አጋርነት እና አመራር ዉጤታማነት ለመለካት የምንጠቀምባቸዉን የክትትል እና ግምገማ (M&E) አመልካቾችን እናያለን፡፡

## 4. የክትትል እና ግምገማ አመልካቾች

የባለድርሻ አካላት ቅንጅት መሻሻልን (እድገትን) ለመለካት ከዚህ በታች የተዘረዘሩ አመልካቾች ግምት ዉስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡

- በስራ ዝርዝሩ መሰረት በተቀመጡ ግልጽ አጀንዳዎች ዙርያ የስብሰባ ቃለጉባዔና የክትትል ተግባርን በማካተት የተካሄደ ባለድርሻ አካላት  የስብሰባ ብዛት፣
- በእያንዳንዱ ስብሰባ የተሳተፉ አጋር አካላት ቁጥር በመቶኛ (%)፣
- ለዉይይት የቀረቡ የሰቆጣ ቃልኪዳን አጀንዎች ብዛት (መጠን)፣
- በሩብ ዓመት የተከለሰ (የተሻሻለ) የዘርፈብዙ አጋር አካላት ቅንጅት መከታተያ መሳርያ (updated Multi-stakeholder mapping tool)፣
- በሩብ ዓመት የተከለሰ (የተሻሻለ) ባለድርሻ አካላት አፈፃጸም ማሳያ ዳሽ ቦርድ (updated Partnership dashboard)፣
- በስብሰባዉ የተገመገሙ ባለድርሻ አካላት  ማሳያ መግለጫ እና የፋይናንስ አጠቃቀም መግለጫ ወይም ማሳያ፣
- ባለድርሻ አካላት  የስብሰባ ቃለጉባዔ በተሰብሳቢወች መፈረሙ በተገቢዉ መልኩ በመሙላት በኦን ላይን (በኤሌክትሮኒክ) የመረጃ ስርዓት ወይም በወረቀት አሰራር መመዝገብ፣
- ሃብት ለማሰባሰብ እና ለመከታተል በተዘረጋዉ ስርአት መሰረት የተዘጋጁ የፋይናንስ ትንታኔ ሬፖርቶች፣
- በሩብ ዓመቱ የተሰሩ የፋይናንስ ክፍተቶች ወይም ግኝቶች ትንታኔ እና በወቅቱ ለክልል መስተዳድር ለማሳወቅ የተላከ ሪፖርት ፣
- በግማሽ አመት (6 ወራት) ዉስጥ የተለዩ እና ለሚመለከታቸዉ አካላት በግብረመልስ ለማሳወቅ የተላኩ  ውሳኔዎች ብዛት፣
- በሰቆጣ ቃልኪዳን ስትራቴጂክ አላማ እና ዝርዝረ ተግባራት መሰረት የተዘጋጀ እቅድ እና በጀት፣
- ማህበረሰብ አቀፍ መማማርያና ሰርቶ ማሳያን ተደራሽ ያደረገ የድጋፍ ብዛት፣

## የክትትል እና ግምገማ ሂደት

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ አገልግሎት ካለ፣ በየጊዜው በሚካሄዱ ስብሰባወች ከሚገኙ ዉሳኔወች በመነሳት የሚታደስ (የሚሻሻል) የኦንላይን ባለደርሻ አካላት አመራር የመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) ዋና ቁልፍ የክትትል ስርዓት መሳርያ በመሆን ያገለግላል፡፡ የፌደራል ፕሮገራመ ማስፈፀም ክፍል፣ የክልል ፕሮገራመ ማስፈፀም ክፍል፣የክልሉ የስርዓተ ምግብ ተጠሪ እና ወረዳ ስርዓተ ምግብ ተጠሪ በቀላሉ በየኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ አማካኝነት የሚሞሉ ማንኛዉንም የሰቆጣ ቃል ኪዳን ባለድርሻ አካላት ቅንጅት እና የፋይናንስ መረጃዎች አፈፃፀም ማሳያወችን (dashboard) ማየት ይችላሉ፡፡ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ተደራሽ ባልሆነባቸዉ አካባቢዎች በወረቀት የሚሰሩ መግለጫወች (ማሳያወች) እና የስብሰባ ቃለጉባዔወች ከክልል ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል፣ ከወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እና ከወረዳ ስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ጋር መረጃ ለመለዋወጥ ያገለግላሉ፡ ፡ የክልል ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል እነዚህን የአፈፃፀም ማሳያወችን በመመልከት ለወረዳወች ግብረመልስ ይሰጣል፡፡

የክልል ፕሮገራመ ማስፈፀም ክፍል እና የክልል ስርዓተ ምግብ ተጠሪ በየ 6ወር በጋራ የአጋር አካላትን ትብብር ሁኔታ ማሳያን ይከታተላሉ፡፡ የፌደራል ፕሮገራመ ማስፈፀም ክፍል ተወካይ ቢያንስ በዓመታዊ የግምገማ ሂደት ወቅት ቢሳተፍ የተሸለ ዉይይት ማስኬድ ይቻላል፡፡ በክትትል ወቅት የተገኙ ሪፖርቶች ለወረዳዉ አስተዳዳሪ እና ለክልል ፕሮገራመ ማስፈፀም ክፍል ሀላፊዎች ይቀርባል፡፡

**ባለድርሻ አካላት የመረጃ ቋት (አፈፃፀም ማሳያ/ መግለጫ)** (Partnership dashboard) በአባሪ ሁለት እንደተገለፀዉ የ አጋር አካላት ቅንጅት ማሳያ (ዳሽቦርድ) ዋና ዋና የአመልካቾች መሻሻልን በማሳየት እንደቁልፍ የአፈፃፀም ማሳያ በመሆን ያገለግላል፡፡ አባሪ B ይመልከቱ፡

## የዘርፈብዙ ሴክተሮች አጋር አካላት ዉጤታማነት መለኪያ ተጨማሪ ቅፆች

ባለድርሻ አካላት ዉጤታማነትን ለመፈተሸ የምንጠቀምባቸዉ ሌሎች ተጨማሪ መሳርያወች አሉ፡፡ በየ ሩብ ዓመቱ የሚገመገምና የሚሻሻል የባለድረሻ አካላት ማጓደን መሳርያ (stakeholder mapping tool) እና የባለድረሻ አካላት ሁኔታ ትንታኔ፣ በየሩብ ዓመቱ የሚገመገም እና የሚሻሻል የፋይናንስ መረጃወች ማሳያ መግለጫ (Financial dashboard)

፤ እነዚህ ሁለቱም የዉጤታማነት መለኪያና መተንተኛ መሳርያወች በአባሪ 10 በተቀመጡት መሰረት በኦን ላይን ባለድርሻ አካላት  ማስተባበር የመረጃ ቋት ስርዓት አካል ናቸው፡፡

**በክትትል ወቅት የምንጠቀምባቸዉ የተግባራት ተፈፃሚነት ማረጋገጫ ነጥቦች (Monitoring checklist)**

የአጋር አካላትን ቅንጅት ማስተባበር ተግባር ለመከታተል ድጋፍ ተኮር የሱፐርቪዥን መርሃግብር በክልል ፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍል እና በክልሉ ቢሮዎች ይዘጋጃል፡፡ ይህ የክትትል ቼክሊስት ዋናዋና አመልካቾችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡ ዝርዝር መረጃዉ በአባሪ ተያይዟል

**በተለያዩ ደረጃወች ያሉ ባለድረሻ አካላት የመረጃ ልዉዉጥና አደረጃጀት የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| በፌደራል ደረጃ | በክልል ደረጃ | በወረዳ ደረጃ |
|---|---|---|
| የተከበሩ ም. ጠ.ሚንስትር<br>• የፌደራል.ፕሮግራም ማስፈፀምያ ክፍል.<br>• ጤና ጥበቃ ምንስተር<br>• ግብርና.ሚንስተር.<br>• ዉሃ.መስኖ ኢነርጂ.ሚንስተር<br>• ትምህርት ሚንስተር<br>• ሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ምንስተር<br>• ፋይናንስ ኢኮኖሚ ሚንስተር<br>• ሴቶች ህፃናት ጉዳይ ሚንስተር | የክልል ርዕሰ መስተዳድር<br>• የክልል ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ክፍል<br>• ጤና ቢሮ<br>• ግብርናቢሮ<br>• ዉሃ መስኖ ኢነርጂ ቢሮ<br>• ትምህርት.ቢሮ<br>• ሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ .ቢሮ<br>• ፋይናንሰ ኢኮኖሚ ቢሮ<br>• ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ.ቢሮ | • ወረዳ አስተዳዳሪ<br>• ወረዳ ጤና ጽሕፈት ቤት<br>• ወረዳ ግብርና ፅሕፈት ቤት<br>• ሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ፅሕፈት ቤት<br>• ትምህርት ጽ.ቤት<br>• ዉሃ መአድን ኢነርጂ ፅሕፈት ቤት<br>• ባለ ድርሻ አካላት የሲቪክ ማህበራት<br>• ሴቶች ህፃናት ጉዳይ ፅሕፈት ቤት<br>• የሃይማኖት ተቋማት ማ.ሰብ ሰርቶ ማሳያ |

| | | |
|---|---|---|
| | | |

## አባሪወች

**አባሪ ሀ**:

**ቢ.ጋር**: የወረዳዉ ስርዓተ ምግብ  አስተባበሪ አካል

**የኮሚቴዉ አባላት**: የሴክተር ፅ/ቤት ተወካዮች፣ ዋናዋና የስርዓተ ምግብ ፈፃሚ የአጋር ድርጅቶች ፣ የማህበረሰብ ላብ ተወካይ

**ሰብሳቢ**: የወረዳዉ አስተዳዳሪ

**አስተባበሪ**: የወረዳዉ ስርዓተ ምግብ ተጠሪ

**የስብሰባ ጊዜ** : በየወሩ

**የኮሚቴዉ ዋና ዋና ተግባራትና ኃላፊነቶች**:

- በወረዳ ውስጥ የስርዓተ ምግብ  ፕሮግራሞችን አጠቃላይ አመራር ይሰጠሉ፤
- ዘርፈ ብዙ አጋር ድርጅቶችን፤  ለጋሽ ድርጅቶችን፣ የመንግስታዊ  እና የግል ፈጻሚ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር ማስተባርና  መምራት፤
- የስርዓተ ምግብ የሀብት ምደባና ትንተና አጠቃቀም  ሪፖርት የከታተላለ
- በወረዳ ውስጥ ለሰቆጣ ቃልኪዳን ቁልፍ ተግባራትን ለመፈፀም የሚያስችል ሃብት ማሰባሰብና አጠቃቀሙን መከታተል
- የሰቆጣ ቃል ኪዳን ስትራቴጂያዊ ዓላማዎችና ተግባራት እንዲሁም የአጋርነት ዳሽቦርድ ጨምሮ አፈጻጸሙን ይገመግማል
- ዋና ዋና የአፈጻጸም ጉዳዮችን በመገምገም የመፍትሄ አቅጣጫዎች ማስቀመጥ
- በአጋር ድርጅቶች መካከል ቅንጅታዊ አሰራርንና ትብብርን ያመቻቻሉ

- አጋር ድርጅቶች በየጊዜው ሪፖርት ለወረዳ እንዲያደርጉ ያመቻቻሉ
- በወረዳዉ የስርዓተ ምግብ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ መስጠት እና ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር ግኑኙነት መገንባት
- የ ሰቆጣ ቃልኪዳን ስትራቴጂ እና ዝርዝር እቅድ ማዘጋጀት፣
- በተለየ ሁኔታ የሰቆጣ ቃልኪዳን ቅንጅታዊ ስራ ውጤታማነት ይገመግማሉ
- ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት፣ማጽደቅ ዓመታዊና የግማሽ ዓመት ሪፖርት መገምገም
- የያንዳንዱን ባለድርሻ አካላት በወረዳ ያለውን ዓመታዊ፤ የሩብ እና ወርሃዊ ዕቅድ መገምገምና የተጠቃለለ የስርዓተ ምግብ ዕቅድ መቀበል
- በወረዳው ውስጥ በስርዓተ ምግብ ዙሪያ የሚሰሩ ባለድርሻ አካላት እና ፈጻሚ ድርጅቶችን ዝርዝር በመያዝ የመረጃ ቋት ማለትም ዳታ ቤዝ መሙላትና እናዳስፈላጊነቱ መከለስ
- መደበኛ የመስክ ጉብኝቶች ማድረግ እና ድጋፍ መስጠት
- የፊዚካልና የፋይናንስ ሪፖርቶችን ማረጋገጥ
- በወረዳ ውስጥ አዳዲስ የአጋር ድርጅቶችን ፣ ፕሮጀክቶችን፣ እና ፕሮግራሞችን ማካተት
- በሴክተሮችና በአጋር ድርጅቶች መካከል የታቀዱ ተግባራትን አፈጻጸም መከታተልና ኦዲት ማድረግ
- የሃብት ልየታና አጠቃቀም ሥርዓትን በየጊዜው መሙላት፣
- የበጀት እና የወጪ ትንተና ውጤት መሰረት ያደረገ ውይይትና ግምግማ በማደረግ ውሳኔ ማሳለፍ
- በሴክተሮች እና በወረዳ ውስጥ ባሉ አጋር ድርጅቶች ተግባር ላይ ያልዋለ ሃብት በመለየት፤ እንዲታቀድ ማድረግ
- የተለዩ ክፍተቶችን ለህዝብ ተዎካዮች፤ ለክልል ማስተባበሪያ፤ የዘርፍ ቢሮዎች እና የክልል ፕሬዚዳንት አማካሪ ማሳወቅ
- የሰቆጣ ቃል ኪዳን ተግባራት ተጨማሪ በጀት እነዲያገኙ፤ ከወረዳ አቅም በላይ ለሆኑ ችግሮች መፍትሔ ማፈላለግና መደገፍ

አባሪ ለ:

- **ሁሉን አቀፍ የባለድርሻ አካላት ማስተባበሪያ እና አጋርነት አስተዳደር ዳሽቦርድ**
- **የመረጃ ክለሳ ጊዜ**: **በየወሩ**

**የሚካሄዱ የስብሰባዎች ዓይነቶች**:

- የስርዓተ ምግብ አስተባባበሪ አካል (NCB): በወረዳ ወይም በክልል
- የስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ (NTC): በወረዳ ወይም በክልል

**የባለድርሻ ትንተና ሪፖርት በሚከተሉትን ቁልፍ አመልካቾች ላይ መሰረት ያደርጋል**

- የስርዓተ ምግብ ላይ ያተኮሩ ፕሮጀክቶች ብዛት እና የሃብት መጠን
- ከስርዓተ ምግብ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ፕሮጀክቶች ብዛት እና ሃብት መጠን
- የሰቆጣ ቃልኪዳን ስትራቴጂክ ዓላማዎች መሰረት አድርገው እየተፈፀሙ ያሉ ፕሮጀክቶች ብዛት
- የ ሰቆጣ ቃልኪዳን ቁልፍ ተግባራት ብዛት
- በኢንቨስትመንት መጠን ወይም ቁርጠኝነት ከፍተኛ አምስት ፈፃሚዎች ዝርዝር
- የሴት ተጠቃሚዎች ብዛት
- ከ2 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናትን ትኩረት ሰጥተው ያካተቱ ፕሮጀክቶችን ብዛት
- የማስፈጸሚያ ሃብትና /የገንዘብ እጥረት

**የፋይናንስ ትንተና**:

ለስርዓተ ምግብ ተኮር እና ተዛማጅ ተግባራት በሰቆጣ ቃልኪዳን አላማዎች፣ በሃብት ምንጭ ፣ በወጪ አይነት በአላማ የተመደበ ጠቅላላ ሃብት፣ በዋና ዋና መለኪያዎች የተቃኘ አፈፃጸም እንዲሁም በበጀት አመቱ ለስርዓተ ምግብ ማስፈፀሚያ በወረዳ የጸደቀ አዳዲስ ፕሮጀክቶች ብዛት:

አባሪ ሐ:

**ቢ.ጋር**: ክልላዊ የስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል

**የኮሚቴዉ አባላት**: የክልል ቢሮ ተወካዮች፣ ዋና ዋና የስርዓተ ምግብ ፈፃሚ አጋር ድርጅቶች፣ ለጋሽ ድርጅቶች፣ እና የግል ተቋማት

**ሰብሳቢ**: የክልሉ ፕሬዚዳንት ወይም የፕሬዝደንቱዋ ተወካይ

**ኣስተባባሪ**: የክልሉ ፕሮገራም ማስተባበሪ ክፍል ፕሮግራም ማኔጀር እና የክልሉ መንግስት የስርዓተ ምግብ ተጠሪ

**የስብሰባ ጊዚያት**:በየሩብ ኣመቱ

**ተግባርና ኃላፊነቶች**:

- በክልሉ ውስጥ የስርዓተ ምግብ ፕሮግራሞች ላይ አጠቃላይ አመራር ይሰጣሉ
- የወረዳ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን መገምገም
- ዘርፈ ብዙ አጋር ድርጅቶችን፤ ለጋሽ ድርጅቶችን፣ የመንግስታዊ እና የግል ፈጻሚ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር ማስተባበርና መምራት፤
- የስርዓተ ምግብ ሀብት ምደባና አጠቃቀም ትንተና ሪፖርት መገምገም
- በወረዳ ውስጥ ለሰቆጣ ቃልኪዳን ቁልፍ ተግባራትን ለመፈፀም የሚያስችል ሃብት ማሰባሰብና አጠቃቀሙን መከታተል
- የሰቆጣ ቃል ኪዳን ስትራቴጂያዊ ዓላማዎችና ተግባራትት እንዲሁም የአጋርነት ዳሽቦርድ ጨምሮ አፈጻጸሙን ይገመግማል

- ዋና ዋና የአፈጻጸም ጉዳዮችን መገምገም ና የመፍትሄ አቅጣጫ ማስቀመጥ
- በአጋር ድርጅቶች መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን እና ትብብርን ያመቻቻሉ
- አጋር ድርጅቶች ወቅታዊ/ቢጊዜው ሪፖርት ለወረዳ እንዲያደርጉ ያመቻቻሉ
- በየአጋር ድርጅቶች መካከል የቅንጅታዊ አሰራርን እና ትብብርን ያመቻቻሉ
- አጋር ድርጅቶች በጊዜው ሪፖርት ለወረዳ እንዲያደርጉ ያመቻቻሉ
- በወረዳዉ ስርዓተ ምግብ ጉዳዮች ላይ ጥብቅና መቆም/ድጋፍ መስጠት እና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ግኙኝነት መገንባት
- የ ሰቆጣ ቃልኪዳን ስትራቴጂ እና ዝርዝር እቅድ ማዘጋጀት፣
- በተለየ ሁኔታ የሰቆጣ ቃልኪዳን ቅንጅታዊ ስራ ውጤታማነት ይገመግማሉ
- ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና በጀት፣ የግማሽ-እና ዓመታዊ ሪፖርት መገምገም እና ማጽደቅ

አባሪ መ:

ቢ.ጋር፣ **የወረዳ የስርዓተ ምግብ ቴክኒክ ኮሚቴ** (WNTC)

**የኮሚቴዉ አባላት**: የሴክተር ፅ/ቤት ፣ ዋናዋና የስርዓተ ምግብ ፈፃሚ የአጋር ድርጅቶች፣ ተጠሪ

ሰብሳቢ: **የወረዳው የግብርና ወይም የጤና**

**የስብሰባው አስተባባሪ**: **የወረዳዉ የስርዓተ ምግብ ተጠሪ**

**የመሰብሰቢያ ጊዜያት**፡ **በየወሩ**

- ለወረዳው ስርአተ ምግብ ማስተባበሪያ አካል ቴክኒካዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል ፣
- የእያንዳንዱን ሴክተር ዕቅድ ማጠናከርና አንድ ወጥ የሆነ የወረዳ ስርዓተ ምግብ ዕቅድ ማዘጋጀት
- ዓመታዊ ዕቅዱን ወደ ሩብ እና ወርሃዊ ዕቅድ በመቀየር ማዘጋጀት፣
- በሰቆጣ ቃል ኪዳን ዕቅዱ ፍኖተ ካርታ መሰረት ተግባርት በበቂ ስፋት እና ጥልቀት የተያዙ ዒላማወችን ለማሳካት በሚችል መልኩ መካተታቸውን ማረጋገጥ
- የሰቆጣ ቃልኪዳን ፕሮጀክቶች ዕቅድ፤ ማሳተባበር፤ መከታተልና፤ መገምገም
- በየሴክተሩና ፈፃሚ ደረጅቶች ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ተግባራትንና ሃሳቦችን መለየት
- ለወረዳ ስርዓተ ምግብ አሰተባባሪ አካል የሩብ ዓመት፤ የግማሽ ና ዓመታዊ ሪፖርት ያዘጋጃል
- ለተጨማሪ የሙከራና ተፈጻሚነት በምርጥ ሃሳቦች ዙሪያ መረጃ መሰብሰብና መሰነድ
- ምርጥ ተሞክሮዎችን ለይቶ ለሚመለከታቸው ያጋራል ወይም RPDU በኩል ለሌሎች ወረዳዎች ያጋራል.

- የማህበረሰብ ደረጃ መማማር,ያና ሰርቶ ማሳያ እና የቀበሌ አስተዳደር ቡድኖች ድጋፍ ይሰጣሉ
- በወረዳው ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች፣ መጠይቆች፣ የተሳሳተ አመለካከት፣ወዘተ ምላሽ እንዲያግኙ ይሰራል
- በከፍተኛ አመራር ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ለወረዳዉ ስርዓተ ምግብ ማስተባበሪያ አካል በማስተላለፍ የውይይት ነጥቦች ለይቶ ይይዛል.
- ምርጥ ልምዶችን፣ የዘርፍ ስኬቶችን በዝርዝር በማዘጋጀት እና የወደፊት እቅድና ትግበራ እንዲጠቅም እዲሁም እውቅና እንዲያገኝ ለወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ማስተላለፍ.

አባሪ ሠ:

**የክልሉ የስርዓተ ምግብ የቴክኒክ ኮሚቴ አደረጃጀት**

**ሰብሳቢ**: በክልሉ መንግስት ፕሬዚዳንት የሚወከል ይሆናል

**የስብሰባው አስተባባሪ / አደራጅ**: የክሉል የስርዓተ ምግብ ተጠሪ እና RPDU ፕሮግራም አስትባባሪ

**የመስብሰቢያ ጊዜ**: በየወሩ

- ለክልሉ ስርአተ ምግብ ማስተባበሪያ አካል ቴክኒካዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል
- የእያንዳንዱን ሴክተር ዕቅድ ማጠናከርና አንድ ወጥ የሆነ ስርዓተ ምግብ ዕቅድ ማዘጋጀት
- ዓመታዊ ዕቅዱን ወደ ሩብ እና ወርሃዊ ዕቅድ በመቀየር ማዘጋጀት፣
- ዕቅዱ በሰቆጣ ቃል ኪዳን ፍኖተ ካርታ መሰረት ተግባራት በበቂ ስፋት እና ጥልቀት የተያዙ ዒላማወችን ለማሳካት በሚችል መልኩ መካተታቸውን ማረጋገጥ
- የሰቆጣ ቃልኪዳን ፕሮጀክቶችን ማቀድ፤ ማሳተባበር፤ መከታተልና፤ መገምገም
- በየሴክተሩና ፈፃሚ ደረጅቶች ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ተግባራትንና ሃሳቦችን መለየት
- ለክልሉ ስርዓተ ምግብ አሰተባባሪ አካል የሩብ ፤ የግማሽና ዓመታዊ ሪፖርት ያዝጋጃል
- ለተጨማሪ የሙከራና ተፈጻሚነት በምርጥ ሃሳቦች ዙሪያ መረጃ ያሰባስባል፤ ይሰንዳል
- ምርጥ ተሞክሮዎችን ለይቶ ለሚመለከታቸው ያጋራል፤ ወይም RPDU በኩል ለሌሎች ወረዳዎች ያጋራል.
- ለወረዳዎች ድጋፍ መስጠት

- በክልሉ ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች፣ የተሳሳቱ አመለካከቶችን፣ወዘተ ምላሽ እንዲያገኙ ይሰራል
- በከፍተኛ አመራር ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ለክልሉ ስርዓት ምግብ ማስተባበሪያ አካል በማስተላለፍ የውይይት ነጥቦች ለይቶ ይይዛል.
- ወረዳዎች የሰቆጣ ቃል ኪዳንን ከሌሎች ፕሮገራሞች ጋር በማገናዘብ እንዲያቅዱና እንዲተገብሩ መደገፍና መከታተል

አባሪ ረ:

**የስብሰባ አጀንዳ……..**

**አጀንዳ……..**

**የወረዳ ወይም ክልል ……..**

**የስብሰባ ቀን……..**

1. የአጋር ድርጅቶች  አፈጻጸም እና አጋርነት ዳሽቦርድ ተግባራዊነት መገምገም
2. የሰቆጣ ቃልኪዳን  ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች እና ዓብይ ተግባራት አፈጻጸም መገምገም
3. በአፈፃፀም ወቅት እያጋጠሙ ያሉ ፈታኝ ሁኔታዎችን ወይም ችግሮች ላይ መወያየት እና ግምገማ / የመፍትሂ ሃሰብ ማመንጨት
4. የባለድርሻ አካላት ዝርዝር መረጃ ቻት ወቅታዊ መደረጉን መገምገም
5. ሀብት ምደባና እና ሀብት አጠቃቀም መገምገም - የፋይናንስ ትንተና ዳሽቦርድ መከታተል
6. አዳዲስ በወረዳች የጸደቁ ፕሮጀክቶች ላይ  ውይይት  ማድረግ
7. በማህበረሰብ መማማርያና ሰርቶ ማሳያ ተግባራት ዙሪያ ማንኛውም ጉዳይ ላይ ይወስናሉ
8. እና ሌሎችም

አባሪ ሰ:

**የሰቆጣ ቃልኪዳን 10 ስትራቴጂካዊ ዓላማዎች**:

1. ከሁለት ዓመት በታች ለሆኑ ሕጻናትን፣ መቀነጨርን ማስወገድ ሥርዓት ምግብ ሁኔታ ማሻሻል
2. አመቱን ሙሉ 100% የምግብ አቅርቦትን ማረጋገጥ
3. የአርሶ አደሩን ምርታማነትና የገቢ ሁኔታ ማርጋግጥ
4. ድህረ ምርት አጠቃቀም ብክነት ዜሮ ማድረግ
5. ዘላቂ የምግብ ስርዓት ማስተዋወቅ፣ ፈጠራን መበረታታት (በአየር ንብረት ዙሪያ)
6. የንጹህ ውሃ ተደራሽነትና የአካበቢ ንፅህና አጠባበቅ ሙሉ ለሙሉ ተደራሽ ማድረግ
7. በትምህርት ቤቶች የህፃናትን ጤናና የአመጋገብ ስርዓተ ሁኔታ ማሻሻል
8. የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የነፍሰ ጡር እናቶችን፣ የሚያጠቡ እናቶችንና ልጆች የአመጋገብ ሁኔታን ማሻሻል
9. የፆታ እኩልነትን ማረጋገጥ፣ ሴቶችን ማብቃት እና የልጆች ጥበቃ ማሻሻል
10. ባለድርሻ አካላትን አቅም ማሰደግ፣ ቅንጅታዊ አሰራርን ማሻሻል

የ ሰቆጣ ቃልኪዳን 50 ስልታዊ ተነሳሽነት ዝርዝር

አባሪ ሸ

የ SD ስልታዊ መተግበሪያ ዝርዝር

1. ማህበረሰቡን መሰረት ያደረገ የአመጋገብ (CBN) ፕሮግራም ተግባራዊ ማድረግ
2. የተጨማሪ ምግብ ፕሮግራሞች ማጠናከር
3. በትምህርት ቤት የአመጋገብና የጤና አገልግሎቶች ማስፋፋት.
4. በማህበረሰብ ደረጃ ተጭማሪ የአመጋገብ የምክር አገልግሎት ተቋም ግምገማ ማካየድ
5. በተመጣጠነ ምግብ እና የጋራ የልጅነት በሽታዎች ቀደም ለይቶ ማዉጣት አስተዳደር እስከ ልኬት ይቀይሩት.
6. አመጋገብ በእናቶች, ልጅ እና የቤተሰብ ዕቅድ, ክትባት እና የልጅነት በሽታዎች አስተዳደር ጨምሮ በጉርምስና የጤና ጣልቃ የመላኪያ አጠናክር.
7. ማኅበራዊ እና የባህርይ ለውጥ መገናኛ (SBCC) ዘመቻ ለመተግበርይገንቡ እና ባለብዙ ሰርጥ
8. አቅም ግንባታ
9. ምርት እና ፍራፍሬ እና አትክልት ፍጆታ መጨመር.
10. ምርት እና ዋና ሰብሎች እንዲሁም በጥራጥሬ ውስጥ ፍጆታ መጨመር.
11. ምርት እና ወተት (በዋነኝነት ፍየል) የወተት ምርቶች ፍጆታ መጨምር
12. ምርት እና ቀይ ስጋ እና የስጋ ምርቶች ፍጆታ መጨምር
13. ምርት እና የዶሮ እና የዶሮ ምርቶች ፍጆታ መጨመር.
14. ምርት እና ዓሣ ዓሣ ምንጭ ምግቦችን ፍጆታ መጨመር.
15. ምርት እና ማር ማር ምርቶች ፍጆታ መጨመር.
16. የእንስሳት መኖ አቅርቦት ማሻሻል
17. የእንስሳት ጤና አገልግሎቶችን ማሻሻል
18. AITCs 20 ሄክታር ያቋቁማል,
19. የሳተላይት ሠርቶ ጣቢያዎች መካከል 0.5 1 ሄክታር መስርት
20. የግብርና ምርቶች የገበያ እድል ፍጠር
21. ዘመናዊ ድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች ያስተዋውቁ
22. የውሃ ቴክኖሎጂዎች እና መፍትሔዎች ባንክ ያቋቁማል,
23. ጨምር የመስኖ አካባቢ ሽፋን

አካላዊ የሆነ ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ጋር መታከም

24. ጨምር ቦታዎች

እድሳት የኃይል ምንጮች

25. ጭማሪ መዳረሻ አጠቃቀምና ሽፋን

26. ጨምር የተጠበቀ እና በቂ ውሃ አቅርቦት ሽፋን

27. ጨምር ጽዳትና ሽፋን

ንፅህና ልምዶችን ያስተዋውቁ

28.

የትምህርት WASH ፕሮግራም 29 ስኬል እስከ

30. ማቋቋም, ተከዜ ወንዝ ተፋሰስ ባለስልጣን

31. በቤት አድጓል የትምህርት ቤት ምግብ ፕሮግራም ያስተዋውቁ

32. የትምህርት ቤት WASH ፕሮግራም ያስተዋውቁ

የትምህርት ቤት የጤና እና የአመጋገብ 33. በስምምነት እስከ ትግበራ

የተከዜ ወንዝ ተፋሰስ ውስጥ ተጨማሪ ወረዳዎች ለመሸፈን 34. ስኬል እስከ ሴፍቲኔት 4

35. ሥርዓተ ፆታና የማህበራዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራሞችን በማስፈጸም ያስተዋውቁ

36. ብድር, እርዳታዎችን, የማይክሮ ፋይናንስ አገልግሎቶች እና ሌሎች የገቢ ማስገኛ ተነሳሽነት አቅርቦት ያስተዋውቁ

ሁሉም ተጋላጭ ቡድኖች መሠረታዊ የአመጋገብ አገልግሎቶች 37. ጨምር መዳረሻ

38. ስኬል እስከ ትግራይ ሶሻል ጥሬ ገንዘብ ማስተላለፍ ፕሮግራም

ሴቶች39. ጨምር የኢኮኖሚ የማብቃት

ሴቶች 40. ጨምር ማህበራዊ የማብቃት

ፆታ ፍትሃዊነት እና የልጆች ጥበቃ ላይ 41. ጭማሪ ማህበረሰብ ግንዛቤ እና ተሳትፎ

42. የልጆች ጥበቃ ያስተዋውቁ

43. በየደረጃው የሴክተር የሥራ ዕቅድ ውስጥ የተመጣጠነ ማቀናጀት

44. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና የሀብት ማሰባሰብ

45. / ያቋቁማል, በሁሉም ደረጃዎች የተመጣጠነ ማስተባበር አካል መዋቅር ማጠናከር

46. እውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር

47. በወረዳ ደረጃ ማህበረሰብ ላብ ማቋቋም,

48. የመጀመሪያው 1000 ሲደመር ማህበራዊ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ማድረግ

49. የፕሮግራሙ ውጤታማ አፈፃፀም ለ PDUs አቅም መገንባት

50. ዲዛይንና እና ጠንካራ አፈፃፀም አስተዳደር ስርዓት ለመተግበር

አባሪ ቀ:

በሁሉም ደረጃ ልንጠቀምበት የምንችል የቃለ ጉባዔ አያያዝ

የወረዳ ስርዓተ ምግብ አስተባባሪ አካል ወይም ስርዓተ ምግብ ኮሚቴ የመደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ

**ቀን በኢትዮጵያ አቆጣጠር : _______________**

ቦታ: _______________

ስብሰባዉ የጀመረበት ሰዓት _______________

ስብሰባዉ ያለቀበት ሰዓት _______________

የተሳታፊ አባላት

1.

2.

3.

ፈቃድ የተሰጣቸው

1.

2.

3.

በስብሰባዉ ያልተሳተፉ

1.

2.

የቀረቡ  አጀንዳ

1.

2.

3.

ቁልፍ የውይይት ጉዳዮች እና ውሳኔዎች

1.

2.

የአጀንዳ  እና የውሳኔ ነጥቦች ማጠቃለያ ጊዜ

| አጀንዳ | ሴክተር / ፕሮጀክት / ፕሮግራም / ፈጻሚ አካል | የቀረበ/የተሰራ | የተለዩ የውይይት ነጥቦች | የተለዩ ዋናዋና ነጥቦች | ኃላፊነት የሚወስደዉ ኣካል | የመጨረሻ ትግበራ/ማስረከቢያ ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|

አባሪ በ:


1. ባለድርሻ አካላት ልየታና ትንተና መሳሪያ(SMT)
2. የፌደራልል ጤና ጥበቃ የተዘጋጀ የማህበረሰብ መማማርያ ና ሰርቶ ማሳያ ሰነድ

አባሪ ቸ:


**ባለድርሻ አካላት ስራ አመራር መረጃ ቓት**

ባለድርሻ አካላት የስራ አመራር መረጃ ቓት (PMDS) የሚያካትተው ባለድርሻ አካላት ልየታና ትንተና፣ መሳሪያ (SMT) የፋይናንስ ምደባ ፣ክትትል፣ አጠቃቀም እና ትንተና መሳርያ የአጋርነት አፈጻጸም መለኪያ ዳሽቦርድ ፣ የክትትል ቸክሊስት የመሳሰሉን ያካትታል ፡፡
በወረዳ ደረጃ የአይቲ ስርዓት በሚሰራበት ቦታ መረጃው በ online የሚሞላ ይሆናል፡፡ ይህ በለሊበት ወረዳዎች ምቹ ሁኒታ እስኪፈጠር ድረስ በማንዋል (በወረቀት ላይ) የሚሰሩ ይሆናል ፡፡

ክልል ወረዳና የሰቆጣ ቃልኪዳን የፕሮግራም ማስተባበሪያ ክፍል online ተግባራዊ ማድረጊያ መመሪያ ይኖራቸዋል ይህ የመረጃ ቃት በክልልና በወረዳ ደረጃ ያለዉን አፈፃጸም ለመከታተልና ቅንጅታዊ አሰራርን ለመገምገም ያስችላል


የወረዳው የባለድርሻ አካላት ልየታ መሳርያ
የባለድርሻ አካላት የትንተና ሪፖርት mapping andanalysis reports
የአድቮኬሲ ተግባራት
የወረዳ On-line የኢጋር ድርጅቶች አስተዳደራዊ ስርአት
የፋይናንስ ዳሽ ቦርd
የኢጋር ድርጅቶች ስብሰባ
የኢጋር አካላት ዳሽ ቦርድ

**ክልላዊ ላይ-መስመር አጋርነት አስተዳደር ሥርዓት: ቅኝት**



ማጣቀሻ:

ልምምድ ውስጥ የተመጣጠነ ምግብ (እሁድ) የሚተልቁ: ርሱ: 2014 Feb በርካታ ባለድርሻ አካላት መሳተፍ

የ ረሃብ ፕሮጀክት: ለሁሉም አቀፍ Advocacy, ያታ-ተኮር, ልማት-መር የማህበረሰብ ልማት, 2014 የካቲት

ብሔራዊ የተመጣጠነ ምግብ ፕሮግራም ባለብዙ ዘርፍ የሆኑ የትግበራ መመሪያ, 2016 ሰኔ

Seqota መግለጫ: ፈጠራ ደረጃ ኢንቨስትመንት ፕላን 2017-2020, 2018 ጥር

ኢትዮጵያ ውስጥ በማህበረሰብ ደረጃ በጤና እና በግብርና ሠራተኞች የተመጣጠነ የስልጠና ማኑዋል; ተስፋዬ ኃይሉ (EPHI), Masresha ተሰማ (EPHI), Mariama Fofanah (ሲ.አይ.ፒ) እና ዘላለም ለማ (ILRI);

የኢትዮጵያ የህዝብ ጤና ተቋም (EPHI), ዓለም አቀፍ ድንች ማዕከል (ሲ.አይ.ፒ) እና ዓለም አቀፍ የእንስሳት ምርምር ኢንስቲትዩት (ILRI)

Seqota መግለጫ: የፌደራል ፕሮግራም መላኪያ ዩኒት; የማህበረሰብ ላብ አፈፃፀም መመሪያ, 2018 ግንቦት

የተመጣጠነ ወደ ባለብዙ ዘርፍ አተያይ: ትንተና እርምጃ ወደ: ፀሐይ ዓመታዊ ለማሰባሰብ, ኒው ዮርክ, መስከረም 2013; Reach በ

ቁልፍ ውሎች የቃላት:

**የማህበረሰብ ሙከራ**: አንድ የማህበረሰብ ላብ አቀራረብ እንደዚህ መሆን እና ስኬታማ የፈጠራ የሚተልቁ በፊት አብራሪ ሚዛን ላይ ለሙከራ ፈጠራዎች በመሞከር እንደ ውስብስብ እና የብዝሃ-ልኬት ችግሮች ፈጠራ መፍትሔ ለማግኘት በትብብር እየሰራ ሁሉ በወረዳ ደረጃ ባለድርሻ አካላት ጋር የተያያዘ አንድ ባለብዙ ዘርፍ መድረክ ነው. የማህበረሰብ ላብ በወረዳና ቀበሌ ደረጃ ላይ ሁለቱም ይመሠረታል.

**ለጋሾች**: ለጋሾች እርምጃዎች መከናወን ለመፍቀድ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣሉ. ቁልፍ ለጋሾች የብዙህን እና የሁለትዮሽ ድርጅቶች, በሚያምነው እና መሠረቶች ማካተት እንዲሁም ደግሞ መንግስት ራሱ ያካትታሉ. አንዳንድ ጊዜ አንድ ለጋሽ ደግሞ ሊባባስ ነው.

**የኢትዮጵያ በጀት ዓመት**: መቁጠሪያው ዓመት ሐምሌ 7 ኛ ለማጥፋት የሒሳብ እና በጀት ዓላማዎች የኢትዮጵያ መንግስት የሚጠቀሙበት ጊዜ,

**ፈጻሚ አጋሮች (የአይፒዎች)**: ፈጻሚ አጋሮች የመንግስት ዘርፍ መንግስታዊ እና ለጋሽ በርካታ ድጋፍ ጋር, አውራ በሆነበት እርምጃ በመተግበር ረገድ ግንባር ድርጅቶች ናቸው.

**የተመጣጠነ ምግብ ሚስጥራዊነት የእርምት እርምጃዎች**የተመጣጠነ-ትብ ጣሌቃ የአመጋገብ ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ያላቸው እና እንደ በግብርና እንደ ጤና ይልቅ በሌሎች ዘርፎች በኩል አሳልፎ ናቸው እነዚህ ናቸው; ትምህርት; እና ውሃ, የአካባቢ ንጽህና, እና ፅዳት ዘርፎች. ምሳሌዎች የምግብ ሰብሎች የህይወት ታሪክ ምሽግ, ሁኔታዊ የገንዘብ ዝውውር, እና ውኃ እና ሳኒቴሽን መሠረተ ማሻሻያዎችን ያካትታሉ. (ምንጭ: USAID); የተመጣጠነ-ትብ ጣሌቃ ዘርፎች ሰፊ ክልል የተመጣጠነ ግቦች እና እርምጃዎች ያካተተ በማድረግ የተመጣጠነ ያለውን መሰረታዊ እና መሠረታዊ ምክንያቶች አንዳንድ መላክ ይችላሉ. በተጨማሪም አመጋገብ-ተኮር ጣልቃ የመላኪያ መድረኮች ሆነው ማገልገል ይችላሉ.

**የአመጋገብ ሃብት**: መርጃዎች አመጋገብ ተኮር እና የተመጣጠነ ስሱ እንቅስቃሴዎች እና ጣልቃ የተመደበው

**የተመጣጠነ ምግብ የተወሰኑ ገብነት**:የተመጣጠነ-ተኮር ድጋፎች እንደ በቂ ምግብ እና የአመጋገብ ቅበላ, አመጋገብ እና የሚንከባከቡ ልምዶችን እና በሽታ ሕክምና እንደ ሕፃን የአመጋገብ የቅርብ የሚወስኑ ለመቅረፍ ሰዎች ናቸው. ምሳሌዎች ጥሩ ህፃን እና ወጣት ልጅ የአመጋገብ, micronutrient ድጎማ እና deworming ማስተዋወቅ ይገኙበታል. (ምንጭ; USAID) .; የተመጣጠነ-ተኮር ገብነት

መመገብ ልማዶች እና ምግብ መዳረሻ እንደ በቂ የአመጋገብ ቅበላ እና መነሻነት የሚቆጠሩ ምክንያቶች መካከል አንዳንዶቹ እንደ የተመጣጠነ ምግብ ያለውን አፋጣኝ መንስኤዎች, አድራሻ

**ዘርፎች**: ሙሉ የ SD ፕሮግራም ለማስፈፀም ለመሳተፍ ቁርጠኝነት ያላቸው የመንግስት ዘርፍ ሚኒስቴሮች.

**አገልግሎት አቅራቢዎች**: የመንግስት ዘርፍ ሚኒስቴር መስሪያ, የፌደራል እና የክልል SD ፕሮግራም አሰጣጥ መለኪያዎች, ለወረዳ አስተዳደሮች, ሴክተር ቢሮዎች እና የአመጋገብ ፕሮግራም አገልግሎት ይሰጣል ይህም ተግባራዊ አጋሮች ናቸው.

**የባለድርሻ**: ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ውስጥ ፍላጎቶች ጋር ሰው, ቡድኖች ወይም ተቋማት. የ SD ያህል, ባለድርሻ በወረዳ እና በክልል ደረጃ ተግባራዊ አጋሮች ያመለክታል

**የባለድርሻ ትንተና**: የባለድርሻ ትንተና ፕሮጀክት ቁልፍ ባለድርሻ አካላት, ያላቸውን አስተዋጽኦ አንድ ግምገማ, እና እነዚህ መዋጮ ፕሮግራም ወይም ብሔራዊ ስትራቴጂ አጠቃላይ አፈፃፀም ላይ ተጽዕኖ መንገዶች መካከል ስልታዊ መለያ ግምገማ ነው.

**የባለድርሻ ካርታ**: አንድ የባለድርሻ ካርታ ውጤቶች ለ ብሔራዊ ስትራቴጂ አፈፃፀም ለመደገፍ ሲሉ ብሔራዊ ፕሮግራም, ያላቸውን ፍላጎት, ወቅታዊ መዋጮ, እና እምቅ ተሳትፎ ውስጥ ባለድርሻ አካላት (ማለትም ተቋማት) ለይቶ አንድ ባለድርሻ አስተዳደር መሳሪያ ነው.

**የባለድርሻ ጉድኝት**:የባለድርሻ ካርታ ለማብራራት እና ብሔራዊ ስትራቴጂ ውስጥ ፍቺ እንደ አስተዋጽኦ ሀብቶች, የቴክኒክ ድጋፍ, እና እንቅስቃሴዎች አፈፃፀም በ በንቃት ብሔራዊ ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ ከተለያዩ ባለድርሻ ለመመደብ ጥቅም ሂደት እና ቨ'ዥዋል መሣሪያ ነው. የባለድርሻ ካርታ ስራ አካላት አስተዳደር ሂደት ጋር መርዳት.

**የባለድርሻ ጉድኝት *መሣሪያ***: ይህ እነርሱ ተሳታፊ ናቸው ቦታ ፕሮጀክት / ፕሮግራም ውስጥ የ SD እና NNP-II, አስተዋጽኦች የእነሱን ደረጃ, እንዲሁም አስፈላጊ አስተዋጽኦ ሰዎች በአንድ በተወሰነ አካባቢ የሚገኙ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ይቀርጻል አንድ መሣሪያ ነው.

**አካላት ተሳትፎ**: ሥራ ፍቺ አድማስ ፍጥረት እና የቅጣት ይመራዋል የሆነ የትብብር ውሳኔ አሰጣጥ እና አፈጻጸም አስተዳደር ሂደት ውስጥ ተሳታፊዎች እንደ ባለድርሻ መጠቀም

**ኃላፊነት ሚኒስቴር**:ኃላፊነት የሚኒስቴር ድርጊት አስተዳደር ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና መውሰድ ሰዎች ናቸው. እነርሱ አመጋገብ-ተኮር ወይም የጤና ጋር የተዛመዱ ናቸው እንደ እርምጃዎች መካከል አብዛኞቹ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሥር ናቸው

**የማቀጨጭ**: አንድ ሕፃን ከታች ጊዜ የማቀጨጭ የሰደደ የተመጣጠነ አንድ ጠቋሚ ነው የሚለካው ነው "ቁመት-ለ-ዕድሜያቸው." የማቀጨጭ የሚከሰተው ሲቀነስ ሚዲያን ቁመት-ለ-ዕድሜ የማጣቀሻ ህዝብ ከ ሁለት መደበኛ የሚያፈነግጡ

**ከማባከን**:ክሳትን አጣዳፊ የተመጣጠነ አንድ አመልካች ነው "ክብደት-ለ-ቁመት" የሚለካው ነው. አንድ ልጅ የማጣቀሻ ሕዝብ አማካይ ክብደት-ለ-ቁመት ከ ሁለት መደበኛ ልዩነቶች ሲቀነስ ከታች ጊዜ የሚያባክኑ የሚከሰተው